## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነ ሰብዕ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ ጥቅል እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስውን የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በሻምቡ አብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት


**በ ሱሴ ተሻለ**


2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብዕ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ ጥቅል እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስውን የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በሻምቡ አብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ ሱሴ ተሻለ

አማካሪ፡ ጌታቸው እንዳላማው (ዶ/ር)

2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**“የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ ጥቅል እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስውን የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ በሻምቡ አብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት”** በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት ጋዜጠኝነትና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ በሱሴ ተሻሌ የቀረበዉ ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲዉን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈታኞች ቦርድ አባላት

**አማካሪ------------------------------------ ፊርማ----------- ቀን---------**

**የዉጪ ፈታኝ--------------------------- ፊርማ----------- ቀን---------**

**የዉስጥ ፈታኝ--------------------------- ፊርማ----------- ቀን---------**

ማውጫ ገጽ

ምዕራፍ አንድ፡ የጥናቱ ዳራ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር ........ 5
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 8
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 8
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 8
ምዕራፍ ሁለት፡ የተዛማች ድርሳናት ክለሳ ........ 9
2.1.የሰዋስው ምንነት ........ 9
2.2.ሰዋስው ማስተማር አስፈላጊነት ........ 9
2.3.ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስውን ማስተማር ........ 10
2.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማስተማር ........ 11
2.5.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎች ንጽጽር ........ 12
2.6.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋሰው ማስተማር . 14
ምዕራፍ ሶስት፡ የጥናቱ ንድፍ ........ 18
3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች ........ 18
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 18
3.3. የጥናቱ ሂደት ........ 21
3.4. የማስተማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት ........ 21
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 22
ምዕራፍ አራት፡ የጥናቱ ዉጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 24
4.1.የውጤት ትንተና ........ 24
4.2.የውጤት ማብራሪያ ........ 27
ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ፤ መደምደሚያና መፍትሄ ........ 29
5.1. ማጠቃለያ ........ 29
5.2. መደምደሚያ ........ 31
5.3. መፍትሄ ወይም አስተያየት ........ 31
ሰንጠረዝ 1፤ በቅድመ ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ........ 24
ሰንጠረዥ 2፤ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ተጠቅሞ ሰዋስው

ማስተማር በጥንድ ናሙና t- ቴስት (paired sample t-test) ፍተሻ..........................25
ሰንጠረዥ3 የተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት....................................................................26
ዋቢጽሁፎች .......................................................................................................... 32
አባሪ 1 .......................................................................................................... 35
አባሪ 2 .......................................................................................................... 50
አባሪ 3 .......................................................................................................... 55
አባሪ 4 .......................................................................................................... 58

# ምስጋና

ጥናቴን በማየት ፈጣን ምጋቤ ምላሽ እየሰጡ ስራዬን ያለምንም መታከትና መሰልቸት በተደጋጋሚ በማየትና በማረም ፈጣን መልስ በመስጠት አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ለዚህ ላበቁኝ ለውድ መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጀት በመመደብና ገንቢ ሀሳቦችን በመስጠት ከጎኔ በመሆን እዚህ ደረጃ ላይ እንድደርስ ስለረዱኝ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል በጣም የምወድህና የማከብርህ ባለቤቴ ደቻሳ ጉሬ ከጎኔ ሆነህ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በማሟላት ለዚህ ቁምነገር ስላደረስከኝ ፈጣሪ የኔ ስላደረገህ አመሰግነዋለው ፡፡ በመጨረሻም ቤተሰቦቼ ስማችሁ እዚህ ያልተጠቀሰ ወዳጆቼ በሙሉ በሀሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ ረድታችሁኝ ለዚህ ስላበቃችሁኝ እኮራባችኋለሁ፤ ውለታችሁን የምመልስ ያድርገኝ፡፡ በሌላ በኩል ለጥናቱ የሚውል አስፈላጊውን መልስ በመስጠት ለተባበራችሁኝ ሁሉ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር በተማሪዎች የሰዋስው እውቀትና ሰዋስው የመማር ፍላጎት ላይ የሚኖረውን ሚና መመርመር ነው። የጥናቱ ተተኳሪዎች በሻምቡ ከተማ አስተዳደር በአብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም. ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ 513 ተማሪዎች 30 ተማሪዎች በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ የተመረጡ ናቸው። ጥናቱ ቅድመ ፍትነታዊ በመሆኑ የተማሪዎቹን የሰዋስው ችሎታና ሰዋስው የመማር ፍላጎት ለማወቅ ቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲፈተኑና የቅድመ ትምህርት ፍላጎታቸውን ለማወቅ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። በመቀጠል የጥናቱን ዓላማ ከግብ ያደርሳል ተብሎ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ለስድስት ሳምንት በሳምንት ሁለት ጊዜ ከፈረቃቸው ውጭ እንዲማሩ ተደርጓል። ከዚያም የጥናቱ ተሳታፊዎች ያመጡትን ለውጥ ለመለካት የድህረ ትምህርት ፈተና እንዲፈተኑና የድህረ ትምህርት የሰዋስው ፍላጎት የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። ለጥናቱ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው በተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ በነዚህ ዘዴዎች አስፈላጊ  የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡ ፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በዳግሞ ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። በውጤት ትንተናው መሰረት የድህረ ሙከራ አማካይ ውጤት(30.77) ከቅድመ ሙከራ አማካይ ውጤት (23.53) በጉልህ በልጦ ተገኝቷል። ይህም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ዕውቀት እንደሚያጎለብት አመላክቷል። የድህረ ትምህርት ፍላጎት አማካይ ውጤት(42.4) ከቅድመ ትምህርት ፍላጎት አማካይ ውጤት(37.05) በልጦ ታይቷል። ይህም ዘዴዎቹን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ላይ ለውጥ እንዳመጣ ያሳያል። በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው በማስተማር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ተጠቅሞ የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀትና ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የድህረ ትምህርት ፍላጎት ተመራጭ እንደሆነ አጥኚዋ ጠቁማለች።*

# ምዕራፍ አንድ

# የጥናቱ ዳራ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቆየት ያለ ታሪክ ያለውን የሰዋስው ትምህርት በተመለከተ አንድ ወጥ አቋም የተያዘ አይመስልም (ኤሊስ፣2006)፡፡ ቶርንስቤሪ (1999) እንደሚያስረዱት ሰዋስውን አስመልክቶ እንደሚካሄደው ክርክር የንድፈ ሀሳብ አመንጪዎችንና የቋንቋ ባለሙያዎችን ያስጨነቀ ጉዳይ የለም፤በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት ታሪክ የሰዋስው ትምህርትን በተመለከተ በተነሱ ድጋፎችና ተቃውሞዎች የተሞላ ነው፡፡

ባትስቶንና ኤሊስ (2009) ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ እንደሆነና ያለሰዋስው እውቀት ቋንቋን በትክክል ለመረዳትና ለማወቅ አይቻልም በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንደኤሊስ (2006) ገለጻ ሰዋስው እውነተኛ ተግባቦት ለመፈጸም የሚረዳ እንጂ የአንድን ቋንቋ ህግ ለመተንተን ብቻ የሚያገለግል አይደለም፡፡

እስከ 1940ዎቹ ሰዋስው ወትርጉም የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን(Grammar Translation Method) መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ህግጋትን እንዲያውቁ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ ነበር፡፡ በሰዋስው ትምህርትም ቀጥተኛ በሆነ መንገድ (deductive Approach) በእያንዳንዱ መዋቅር የቅርጽ ልዩነት ላይ ግልጽ ትንተና ይካሄድ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ በእዝን ወአፋዊና በሁነታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ (Situational Language teaching Method) ሲተካና ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተቀባይነት እያገኘ ሲመጣ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለሰዋስው ትምህርት ሲሰጠው የነበረው ትኩረት እየቀነሰ መጥቷል (ራዘርፎርድ፣1987)፡፡

ኤተር (2012) ሪቻርድስና ሮጀርስ (2001)ን ዋቢ በማድረግ እንደሚያስረዱት ከታወቁ የሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ አንዱ ነው፡፡ ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ ከ19ኛው እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አገልግሎት ላይ ሲውል የነበረ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴም ከግሪክና ከላቲን የማስተማሪያ ዘዴዎች የተገኘ እንደሆነና ሰዋስውንና ቃላትን አውዳዊ ባልሆነ መልኩ የመተርጎም (decontextualised translation) ተግባር ሚታይበት ነው፡፡ ትኩረቱንም የጽሁፍ ቋንቋ ላይ ብቻ ያደረገና፣ የንግግር ቋንቋን የማያጠቃልል

የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑ ከሌሎቹ የማስተማሪያ ዘዴዎች ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከ1950ዎቹ እስከ 1980ዎቹ በቋንቋ ማስተማር ታሪክ ሌሎች ታዋቂ የማስተማሪያ ዘዴዎች ብቅ ያሉበት ዘመን እንደሆነ ሪቻርድስና ሮጀርስ (2001) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ወቅት የቀጥተኛ ዘዴ (direct method)ና የእዝን ወአፋዊ ዘዴ (audiolingual method) ነበር፡፡ ቀጥተኛ ዘዴ ተማሪዎች በተተኪሪው ቋንቋ እንዲናገሩና እንዲያስቡ የሚደረግበት የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች የመጀመሪያ ቋንቋቸውን በብቃት በሚማሩበት መንገድ የሁለተኛ ቋንቋቸውንም ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲማሩ በማስመሰል/በመኮረጅ (immitation) ይቀርብበታል፡፡

እንደ ሪቻርድስና ሮጀርስ (2001) ገለጻ ተማሪዎች በእዝን ወአፋዊ ዘዴ ቋንቋውን እንዲማሩ የሚደረገው በድግግሞሽና የባህርያዊያንን መርህ በመከተል ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በማድረግና ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ትምህርቱ ይቀርባል፡፡ በምልልስ (dialogue) ተተኪሪውን ቋንቋ መለማመድ የቋንቋውን ንበት (pronounciation) እና የቋንቋውን ሰዋስው በትክክል ለመለማመድ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሆኖም በቪጎትስኪ ማህበረ-ባህላዊ ንድፈ ሀሳብ (vygotsky socio-cultural  theory) ሰዎች ቋንቋን ለመማር ወሳኙ ነገር መስተጋብር እንደሆነ ከተገለጸ በኂላ የእዝን ወአፋዊ ዘዴ ጥያቄ ውስጥ ገባ፤ የዘዴው ውጤታማነትም ጥርጣሬን እየጫረ መጣ፡፡ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ጥንታዊ ዘዴ (traditional method) በተግባቦታዊ አቀራረብ ተተካ፡፡ ይህ ዘዴም እስካሁን በተለይ በውጭ ቋንቋ ማስተማር የበላይነትን ይዞ ይገኛል፡፡ ተግባቦታዊ አቀራረብ (communicative approach) ቋንቋን ለእውነተኛ ተግባቦት እንዲበቃ የሚያደርግ ሀሳብ በማሳደግ ላይ እንደሚያተኩር ባለሙያዎቹ ያስረዳሉ (ኤተር፣ 2012)፡፡

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ተግባቦታዊ ዘዴ የቋንቋን መዋቅር ከመግለጽ ይልቅ በቋንቋው መግባባት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማመላከት ላይ የሚያተኩር ዘዴ ነው፡፡ ላይትቦውንና ስፓዳ (2006) እንደሚያስረዱት መዋቅሮችን ተራ በተራ ማቅረብ ቋንቋን በሚገባ ለማለማመድ አያስችልም፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደትም በመጀመሪያ በሚገባ መግባባት ለመቻል (fluency) ትኩረት ሰጥቶ ተማሪዎችን ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ልምምድ ተከትሎም ትክክለኛነትን (accuracy) ለማምጣት መስራት ይገባል፡፡እንደ ስፓዳና ላይትቦውን አገላለጽ ተማሪዎች በተግባቦታዊ ዘዴ ሲማሩ በቋንቋው እውነተኛ (authentic) አጠቃቀምን ያዳብራሉ፡፡

የተግባራዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ (Functional Language Theorist) አራማጆች እንደሚገልጹት ቋንቋ ተግባቦት መፍጠሪያ እንጂ የቋንቋው መዋቅር አይደለም (ሀሊዴይ፣ 2004፤ ዊልከንስ፣ 1976፤ ዊዶውሰን፣ 1978)። እንደ እነዚህ ባለሙያዎች አገላለጽ የቋንቋ ትምህርት አላማ ተግባቦት እንዲፈጠር ማስቻል ነው። የሰዋስው ትምህርት ይህን የቋንቋ ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል ስልት መቅረብ ይኖርበታል።ሰዋስውም በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ካለው ግልጋሎት አንጻር ሊፈተሽ ይገባል።

የሰዋስውን ትምህርት በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ከሚያስችሉ ስልቶች አንዱ ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን የማስተማር (inductive approach) አቀራረብ ነው። ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስተማር አቀራረብ የቋንቋውን መዋቅር በቀጥታ ከመግለጽ ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ተማሪዎች ህግጋቱን ፈልገው እንዲደርሱባቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል (ኑናን፣1999፣ ክራሽን፣ 1982)።

ፊስቸር (1979) እንደሚያስረዱት ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ መምህሮቻቸው በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ከሚቀርቡላቸው ሞዴል አረፍተ ነገሮችና ጽሁፎች ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ህግጋትን እንዲያፈልቁ የሚያስችል አቀራረብ ነው። ይህም ከመምህራን በሚያገኙት መጠነኛ ድጋፍ ተማሪዎች ለራሳቸው ሰዋስዋዊ ህግጋትን ፈልገው የሚደርሱበትን ሁኔታ ያሳያል። ምካይ (1987) እንደሚገልጹት ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስተማር አቀራረብ ተማሪ-ተኮር የሆነና ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ በጥልቀት እንዲያስቡ የሚያስችላቸው ስልት ነው።

ራዘርፎርድ (1987) ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን የማስተማር ዘዴ መሰረት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ቋንቋ "ሀሳብ ለመለዋወጥ የሚያስችል ስልት ነው" (Means for communicating ideas) የሚል አመለካከት እንዳላቸው ያስረዳሉ። በመማር ማስተማር ሂደት ለቋንቋ ቅርጽ የሚሰጠው ትኩረት ቋንቋን ለመማር በቂ ወይም አስፈላጊ ሁኔታ አይደለም (ራዘርፎርድ፣ 1987)።

ሀርመር (1987) ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስ

ተማር አቀራረብን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤ ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስተማር አቀራረብ ምንም እንኳን ተማሪዎች ቋንቋውን እየተማሩ ሰዋስዋዊ እውነታዎች ለተማሪዎች ይፋ የማይሆኑበት አቀራረብ ነው። በሌላ በኩል ተማሪዎች የመረጃ ክፍተት ያሉባቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ወይም የሚቀርበውን አዲስ ሰዋስዋዊ ህግ የያዘ መጽሐፍ እንዲያነቡና

ከቀረበላቸው መጽሐፍ ሰዋስዋዊ ህግጋትን እንዲረዱ የሚደረግበት ስልት ነው (ሀርመር፣ 1987)፡፡

ክራሽን (1982) እና ቶርንስቤሪ (1999) እንደሚያስረዱት ህጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን የሚለምዱበት ሂደት እና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በትምህርትነት የሚቀርብላቸውን ሰዋስዋዊ ይዘት በአንድምታዊ አቀራረብ የሚማሩበት ስልት ተመሳሳይ ነው፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች (የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን የሚለምዱ ህጻናት እንዲሁም ሰዋስውን በአንድምታዊ አቀራረብ የሚማሩ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች) የቋንቋ ለመዳን ለሚያመቻቹ በርካታ ተለማጅ ግብዓቶች እንዲጋለጡ ይደረጋል፡፡ ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስተማር አቀራረብ አብዛኛው የመማር ማስተማር ጊዜ  የሚሸፈነው በተማሪዎች ንግግር ሲሆን የማስተማሪያ ዘዴው ከመምህር መራሽነት ይልቅ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ያስችላል(ቶርንስቤሪ፣1999)፡፡

ከዚህ ጋር በተዛመደ ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በቀጥታ ለቋንቋ ህግጋት የማይጋለጡበትና ባላቸው ልምድ መሰረትነት የቋንቋ ህጎችን ፈልገው እንዲደርሱባቸው የሚያደርግና ተማሪዎቻቸው ለሚፈጥሩት ሰዋስዋዊ ስህተት መምህራን አሉታዊ ግብረ መልስ እንዲሰጡ የማይጠበቅበት አቀራረብ እንደሆነ (ሪቻርድስና እስኪሚዲት፣ 2002) አመላክተዋል፡፡ ከዚህ ብያኔ ዊዶዶ (2006) እንደሚያስረዱት ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን ማስተማር አቀራረብ ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ሊተካ የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

አልጋዛሊ (2006) ቫርኬይን (1995) ዋቢ አድርገው እንደሚገልጹት ከታወቀ ነገር በመነሳት ያልታወቁ ሰዋስዋዊ ህግጋትን የሚያቀርበው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፤

1. ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩና ሁሉንም ነገር ከመምህሮቻቸው እንዳይጠብቁ ያደርጋቸዋል፤
2. ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ከተለያዩ  ምሳሌዎች ሰዋስዋዊ ህግጋትን ፈልገው የማውጣት ጥረት እንዲያደርጉ ይጠይቃል፤ በመሆኑም ተማሪዎች ለራሳቸው ፈልገው የሚያገኙት ሰዋስዋዊ ህግ አይረሴ ይሆናል፤
3. ተማሪዎች አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
4. የመማሪያ ክፍሉ አስደሳችና በተለያዩ ተግባራት የተሞላ እንዲሆን ያስችላል፤

ከላይ ለመቃኘት እንደተሞከረው የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም አቀራረቡን በተመለከተ ሁሉንም ባለሙዎች የሚያስማማ አንድ ወጥ አቋም የለም፡፡

ማሬው (2003፣ 43) ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን ማስተማር ዘዴዎችን በተመለከተ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> እነዚህን ሁለት ብልሀቶች አንደኛውን ከሌላኛው አማርጦ ብቻውን ወይም አጣምሮ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሁለቱን ብልሀቶች አንዱን ከሌላው አማርጦ ወይም በጥምረት ለመጠቀም ቋንቋውን የሚማሩት ተማሪዎች ሁኔታና ለትምህርት የሚቀርበው ሰዋስው ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ አዋቂዎች ሆነው ከልዩ ልዩ የአካዳሚክ መስኮች ጋር ትውውቅና ብስለት ያላቸው ተማሪዎች ለምሳሌ የሰዋስው ህግጋትን ማብራሪያ ከመምህሩ ይጠብቃሉ፤ ያደንቃሉም፡፡ በዳራዊ ልምዳቸውና በትምህርታቸው ብስለት ለሌላቸው ግን ያለሰዋስዋዊ ህግጋት ማብራሪያ ከታወቁ ነገሮች በመነሳት ያልታወቁ ሰዋስዋዊ ህግጋትን ማስተማር ውጤታማ ነው፡፡

በአጠቃላይ በቋንቋ ትምህርት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አስመልክቶ የሚካሄዱ ጥናቶች የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋስው በክፍል ውስጥ ለማቅረብ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የቋንቋ መምህር በይዘትነት የተመረጠውን ትምህርት ወደ ክፍል ይዘው ሲገቡ ትምህርቱን በትክክል ከተማሪዎች ዘንድ ያደርስልኛል ብለው የሚያስቡትን ማቅረቢያ ዘዴዎች መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ለትምህርት የተዘጋጀውን የሰዋስው ይዘት ለማቅረብ የትኛው የማቅረቢያ ዘዴ ውጤታማ ነው የሚለው ሀሳብ በጥናት ሊፈተሽ ይገባል፡፡ ይህ ጥናትም ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና ይመረምራል፡፡ ለዚህም የቋንቋ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሊፈተሽ ይገባል፡፡ ይህ ጥናትም ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች ያላቸውን ፋይዳ በመመርመር ላይ ያተኩራል፡፡

### 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

ከገሀዳዊ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንጻር ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ በነዚህ ምሳሌዎች መነሻነት ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ህግጋትን ፈልገው እንዲደርሱባቸው የሚያደርግ ነው፡፡

ላይትቦውን (2006) የቾምስኪን ሀሳብ በመጋራት፤"በተግባቦታዊ ሂደት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም የሰሟቸውን አረፍተ ነገሮች ብቻ አያዋቅሩም፤ ከዚህ ይልቅ በሚያዋቅሯቸው አረፍተ ነገሮች አዳዲስ ፈጠራዎችን ይጨምራሉ፡፡ ስለዚህ ቋንቋ የሚለመደው አስመስሎ በመናገር አይደለም፤" የሚል አቋም አላቸው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ብቃት (Grammatical Competence) እንዲኖራቸው ለተለያዩ ምሳሌዎች የተጋለጡ መሆን አለባቸው (ስኪዎርትዝ፣1993)፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ባይሆን ተቀራራቢ ግንኙነት ካላቸው በሀገር ውስጥ ከተሰሩ ጥናቶች የመለሰ (2008) ጥናት አንዱ ነው፡፡

የመለሰ (2008) ጥናት አላማ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት መዳሰስ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በምስራቅ እና በምዕራብ ሸዋ ዞን የሚገኙ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ አካባቢና በጥናቱ ተሳታፊዎች ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ በመለሰ (2008) ጥናት በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ለከዝርዝር ወደ ጥቅል የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አወንታዊ አመለካከት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን አስመልክቶ የቋንቋ መምህራን ያላቸውን አመለካከት መፈተሽ ብቻ ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ አያስችላቸውም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ማረው(1998ዓ.ም) የሰዋስው ትምህርት አላማን አስመልክተው "የሰዋስው ትምህርት አቢይ አላማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ከማስቻል ውጭ አይሆንም ፡፡" ይላሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ለተማሪዎች የሚያቀርቡበት ስልት ምን እንደሚመስልና አቀራረባቸው የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡ የመለሰ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በሰዋስው ትምህርት ላይ በሚደረግ ጥናት ቢመሳሰልም በጥናቱ ዋና ዓላማና በጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሁም ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

በአጠቃላይ በርካታ አማርኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በአብዛኛው የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት እውቀታቸው የሚፈለገው ያህል አለመሆኑና በሰዋስዋዊ ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት እያስመዘገቡ እንደሆነ አጥኚዋ በ23 ዓመት የማስተማር ልምድ ግንዛቤ አግኝታለች፡፡ ከዚህም ባሻገር ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ብዙም ትኩረት ያልሰጡ በመሆኑ ይህ ጥናት የአማርኛን ቋንቋ ሰዋስው የሚማሩ ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ

ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ ያለውን ሚና በመመርመር ላይ እንዲያተኩር ምክንያት ሁነዋል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ይጨምራል/ያጎለብታል ወይ?
2. ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት ያጎለብታል ወይ?

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ ጥቅል እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አለው፡፡

1. ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ተጽዕኖ መፈተሽና
2. ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ተጽዕኖ መፈተሽ ነው፡፡

### 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረባቸውን እንዲፈትሹ ይረዳል፡፡
2. አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር እንደሚቻል መረጃ ይሰጣል፡፡
3. ወደ ፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች ሰዋስውን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ከማስተማር አንጻር መረጃ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ አካባቢ በኦሮሚያ ክልል በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን በሻምቡ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አቢሼ ገርባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በሻምቡ ከተማ ከሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥናቱ በአቢሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡በሌላ በኩል የዚህ ጥናት ትኩረቱ ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀትና የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ብቻ ላይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1.የሰዋስው ምንነት

የሰዋስውን ምንነት አስመልክቶ የሚሰጡ ብያኔዎች የተለያዩ ከመሆናቸው ባሻገር ጽንሰ ሃሳቡን በተመለከተ ቁርጥ አድርጎ ይህ ነው ብሎ ለማለት አይቻልም፡፡ በተለያዩ አውዶች ውስጥ የተለያየ ብያኔ ያለው በመሆኑ እንደ ሁኔታው ይቀያየራል ፡፡ ያም ሁኖ ሰዋስውን በተመለከተ የሚከተሉት ብያኔዎች ተሰጠዋል፡፡ ግሪን ባውማ (1988) እንደሚያስረዱት ሰዋስው የስነ ልሳን ጥናት አንዱ ክፍል ሲሆን የሚያጠናውም የቃላት ክፍሎችን፣ የድምጽ አፈጣጠር ሁኔታን፣ ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን ግንኙነትና ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስነ ድምጽን፣ የአጻጻፍ ስርዓትንና ስነ ፍቺን ያጠቃልላል፡፡

ባየ (1987ዓ.ም) ሰዋስው የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ እንደሚከተለው ያብራራሉ፤ “ሰዋስው የሚለው ቃል በግዕዝ መሰላል ማለት ነው፤ መሰላል ከአንድ አነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ቀስ በቀስ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ የአማርኛ ሰዋስው ሲባል የአማርኛን ድምፆች አይነት፣ አፈጣጠርና አቀነጻጀት፣ የአማርኛን ቃላት አይነት፣ አመሰራረትና አቀነጻጀት፣ እንዲሁም የሀረጋቱን አይነትና የአወቃቀር ስርዓት ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ የእውቀት ዘርፍ ማለት ነው፡፡ ድምፅ ከድምፅ ጋር ተቀናጅቶ ቃልን፤ ቃል ከቃል ጋር ተጣምሮ ሀረግን፤ እንዲሁም ሀረግ ከሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገርን ደረጃ በደረጃ የሚፈጥርበትን ስርዓት የሚመለከት ጥበብ ነው (ባየ፣ 1987 ዓ፣ም)፡፡

## 2.2. ሰዋስው ማስተማር አስፈላጊነት

ኤሊስ (2002)ና ስካሃ(1998)ን በመጥቀስ መሀመድና ሌሎች (2008) እንደሚያስረዱት የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሰዋስው ትምህርት ላይ ላለፉት 2000 አመታት በላይ ክርክሮች ሲነሱ ነበር፡፡ ክርክሮቹም የሚያተኩሩት፣ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስው ማስተማር ተቀዳሚ ዓላማ ሊሆን ይገባል የሚሉ በአንድ ወገን፣ የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋ ትምህርት መወገድ አለበት የሚሉ በሌላ ወገን፣ በተጨማሪ ጥንታዊ የሰዋስው ትምህርት ትርጉምን

መሰረት ማድረግ አለበት፤ በሚሉ ሀሳቦች ላይ ከፍተኛ ክርክር ነበር። ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት የሁለተኛ ቋንቋ መምህራንንና አጥኚዎችን ቀልብ የሳበ ነው።

ናሳጅና ፎቶስ (2004)ን በመጥቀስ ባለሙያዎቹ (መሀመድና ሌሎች፣ 2008) እንደሚያስረዱት በሁለተኛ ቋንቋ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ የሰዋስው ትምህርት ሚና በሁለተኛ ቋንቋ መማር ላይ ያለውን አስተዋጽኦ ከግምት ያስገባ ነው። በተወሰኑ ሰዋስው ቅርጾች ላይ በማተኮር ለተግባቦት በሚውል መልኩ ሰዋስው ማስተማር ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ በትክክል ለመጠቀምና ደረጃቸውን እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል። በተመሳሳይ ሀሳብ ዳውቲይ (2001)ና ኤሊስ (2002) እንደሚያመለክቱት በተተኳሪው ቋንቋ ቅርጽና መዋቅር ላይ ትኩረት አድርጎ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን መግባባት አቅም ለማጎልበት ያስችላል። ይህም በቋንቋ ትምህርት በተግባር የተፈተነና የመማሪያ ክፍልን መሰረት ያደረገ ጥናት አመልክቷል (መሀመድና ሌሎች፣ 2008)።

## 2.3. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስውን ማስተማር

ዴኮ (1996)ን በመጥቀስ መሀመድና ሌሎች (2008) እንደሚያስረዱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስውን ማስተማር ማለት በመጀመሪያ የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋስው ህግ በመምህሩ አማካኝነት ማስተዋወቅና ከዚያም በተማሪዎች በተግባር እንዲውል የማድረግ ዘዴን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማቅረብ ዘዴ ነው። ይህም ከላይ ወደ ታች (Top Down) አቀራረብን ያመለክታል። ማውተን (2004) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በሚፈጽሙት ተግባር በፍጥነትና በትክክል የሚያጋጥማቸውን ችግር እንዲፈቱ የማስቻል አቅም አለው በማለት ይገልጻሉ። ዩኒይ (1974) እንደሚያስረዱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ አስቀድሞ የተተነበየ ነው። ምክንያቱም የሚቀርበው መረጃ በመምህር የሚመረጥና የአቀራረቡም ሂደት በመምህር ብቻ የሚወሰን ነው። ሻፈር (1989) በአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ላይ ትችት አቅርበዋል። ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ ሰዋስዋዊ ህጎችን በተግባር ላይ የማዋል ችግር እንዲያጋጥማቸው መንገድ ይከፍታል። ከዚህ በተጨማሪ የሰዋስው ትምህርት በትርጉም ላይ ደካማ ተሳትፎ እንዲኖረው፣ተማሪዎችም በንቃት መሳተፍን እንዳያዳብሩ ያደርጋል (መሀመድና ሌሎች፣ 2008)።

ጎነርና ሌሎች (1978)ን ዋቢ በማድረግ መሀመድና ሌሎች (2008) እንደሚያስረዱት የአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ በውጤታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉ ተማሪዎች ዘንድ

ውጤታማ ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር እንዲያውቁም ያግዛቸዋል፡፡ ጥንታዊ የመማር ዘዴን በለመዱ ተማሪዎችም ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡ ስክራምፐፈርና ስፓክ (2005) አንድ ፕሮግራም አስተዋውቀዋል፡፡ ፕሮግራሙም ማቅረብ፣ መተግበር፣ ማመንጨት፣ መገምገም (Presentation-Practice-Production-Evaluation) የሚል ሲሆን የተመሰረተውም በአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ባህርይ ላይ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ሰዋስው ማስተማር የተጠቃሚውን አቅም ማጎልበትና የቋንቋውን ሰዋስው ህግ እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው፡፡

## 2.4. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማስተማር

ማውንተን (2004)ን በመጥቀስ መሀመድና ሌሎች (2008) እንደሚያስረዱት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ የቋንቋውን አውድ መሰረት በማድረግ የተተኳሪውን ቋንቋ ህግ በተግባር የተደገፈ ምሳሌዎችን በመገልገል ማቅረብን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የዚህ ዘዴ ሂደት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ምሳሌዎችን በማመንጨት ከምሳሌዎቹም በመነሳት ተማሪዎች ወደ አጠቃላይ ህግ በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ የሚያግዝና የመምህር እገዛም ወደህጉ ለመድረስ አስተዋጽዖ የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡

አውሱበል (1963)ና ካሮል (1964)ን ዋቢ በማድረግ ባለሙያዎቹ (መሀመድና ሌሎች 2008) እንደሚያስረዱት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች አስቸጋሪ ነው፡፡ በሌላ በኩል በትምህርታቸው ጠንካራ የሆኑ ተማሪዎች ከቀረቡት ምሳሌዎች መዋቅሮችን የማመልከት ችሎታ አላቸው፡፡ ከዚህ ሀሳብ በተለየ ሁኔታ በሻፈር (1989) ጥናት እንደተመለከተው በትምህርታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ተጠቃሚ እንደሆኑ አመልክተዋል፡፡ ዩኒይስ (1974) እንደሚያስረዱት ከተለያዩ ጥናቶች መካከል የተወሰኑት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ አንድን ነገር ሳይረሱ እንዲቆዩና እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል በሚልና የቃላትንና ሰዋስዋዊ ቅርጾችን ትርጉም ለመረዳትና የማስታወስ ችሎታ እንዲዳብር ያደርጋል በሚል ምክንያት ዘዴውን የሚደግፉ አሉ፡፡

ብሉይደርን (1989)ና ሻፈር (1989) እንደሚገልጹት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ አዋቂዎችን በጥንታዊ ቋንቋ (Classical Language) ሳይሆን በዘመናዊ የውጭ ቋንቋ (Modern foreign languages) ጭውውት ችሎታ (conversational ability) በማስተማር ሂደት ውጤታማ ነው፡፡ በአጥኚዎች ዘንድ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ ስለመሆኑ

ስምምነት አለ። ነገር ግን ተማሪዎች የራሳቸው አእምሯዊ ችሎታ ላይ ተመስርተው ቀደምት መረጃዎችን በተግባር ላይ በማዋል በኩል አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ ሊኖር ይችላል (መሀመድና ሌሎች፣ 2008)።

## 2.5. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎች ንጽጽር

መሀመድና ሌሎች (2008) እንደሚያስረዱት የመምህር ትምህርት አቀራረብ በሰዋስው ትምህርት ሂደት ትልቅ ሚና ይጫወታል። ይህም ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት እንዴት እንደሚረዱና በትክክል እንዴት እንደሚጠቀሙ በማድረጉ ሂደት ጠቃሚ ሚና አለው። በዚህም ምክንያት ነው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎች ሰዋስው ማስተማር ላይ ፍላጎት የታየው። የተወሰኑ ቀደምት ጥናቶች እንዲከለሱና በሁለቱ ዘዴዎች መካከልም ያለውን ንጽጽር እንዲሁም በዘዴዎቹ ጠንካራና ደካማ ጎን ላይ ለማተኮር ምክንያት የሆነው።

ሁለቱን ዘዴዎች በማነጻጸር ሂደት ውስጥ አንደኛው ልዩነት፣ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ዘዴ በቋንቋ ማስተማር ሂደት ከሰዋስው ወትርጉም ዘዴ (grammar-translation) ጋር ይመሳሰላል። በሌላ በኩል ከዝርዝር ወደአጠቃላይ ዘዴ ከአዳምጦ መናገር ዘዴ (audio-lingual) ጋር ይመሳሰላል (ጎሊን 1998)። በተመሳሳይ ሀሳብ ሻፈር (1989) እንደሚገልጹት ከዝርዝር ወደአጠቃላይ ዘዴ ከአዳምጦ መናገር ዘዴ ጋር ይመሳሰላል። በዚህ ዘዴ መምህር በክፍለ ጊዜ መጨረሻ ለተማሪዎች ትክክለኛውን ህግ ያቀርባል (መሀመድና ሌሎች 2008)።

በሁለቱ ዘዴዎች መካከል የሚታየው ሁለተኛው ልዩነት የእያንዳንዳቸው አካሄድ ነው። ዩኒየል (1974)ን በመጥቀስ ባለሙያዎቹ (መሀመድና ሌሎች 2008) እንደሚገልጹት የከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ህጎችን በማቅረብና በማስተዋወቅ ይጀምራል። ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ግን የቋንቋውን አውድ መሰረት በማድረግ ህጎችን በማቅረብ ላይ ያተኩራል። ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ሂደት ሀሳቦች የሚመነጩት ከአጠቃላይ (generalization)፣ ከመርሆች (principles)፣ ህጎች (rules)፣ ስርአቶች (laws)፣ ሀሳቦች (propositions) ወይም ንድፈሀሳቦች (theories)ና ከታወቁ ተግባራት ነው። በዚህ መሰረት የዲዳክቲቭ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ምሳሌዎች መጓዝን ያመለክታል።

እንደ መሀመድና ሌሎች (2008) ገለጻ ሶስተኛው ልዩነት የሚያተኩረው ሰዋስው በመማር ማስተማር ሂደት አንድምታዊነት (implicit) እና ገሃዳዊነት (explicit) ላይ ነው። ባለሙያዎቹ ዶኔትና አይደር ሀውክ (1992)ን ዋቢ በማድረግ እንደሚያስረዱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

ዘዴና ገሃዳዊነት በመምህር ገለጻ የሚቀርቡ ሲሆን በዝርዝር ወደ አጠቃላይና አንድምታዊነት መካከል ያለው ግንኙነት ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ማድረግ ላይ ነው፡፡

ቻውድሮን (1988) እንደሚያስረዱት በገሀዳዊና አንድምታዊ የማስተማር ስትራቴጂ ንጽጽር ላይ ያተኮሩ ጥናቶች በብዛት የተካሄዱ ሲሆን ከሚገለጸው ውጤት አንጻር ሲታይም የአንድምታዊ አቀራረብ ውጤታማነት የበለጠ እንደሆነ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ሊትልውድስ (1975) እንደሚያስረዱት የሰዋስው ገሀዳዊነት አቀራረብ ከሚከተሉት ሁለት መንገዶች በአንዱ ሊወሰን ይችላል፡፡

1. ህጉ አጠቃላዩን ባህርይ ሲያመለክት
2. በገለጻ አማካኝነት የህጉ ትዕዛዝ ቋንቋን በመጠቀም ሂደት ከየት መጀመር እንዳለበት ሲያመለክት ነው (መሀመድና ሌሎች 2008)፡፡

ዕድሜ አራተኛው የሁለቱ ዘዴዎች ማነጻጸሪያ እንደሆነ ባለሙያዎችን ዋቢ በማድረግ መሀመድና ሌሎች (2008) ይገልጻሉ፡፡ ሪቨርስ (1975) በጥናታቸው ውጤት እንዳመለከቱት በጥቅል ዘዴ ማስተማር አብዛኛውን ጊዜ ውጤታማ የሚሆነው ለአዋቂዎችና ጥሩ ተነሳስኦ ላላቸው ወጣት የቋንቋ ተማሪዎች ወይም እድሜያቸው ከፍ ላለ ሰዎች ነው፡፡ በርግጥ በሪቨርስ ከቀረበው የተማሪዎች እድሜ መረዳት እንደሚቻለው ለሁለቱ ዘዴዎች ወሳኝ የሆነ የተማሪዎች እድሜ ይሄ ነው ተብሎ ትክክለኛው በአሀዝ አለመገለጹን ነው፡፡

አምስተኛው የሁለቱ ዘዴዎች ልዩነት አመልካች የሆነው ጊዜ ነው (መሀመድና ሌሎች 2008)፡፡ ዩኒይ (1974)ን በመጥቀስ ባለሙያዎቹ እንደሚያስረዱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ፈጣንና ሰፊ እውነታዎችን በአንድ ጊዜ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ ህጎችን በገለጻ ማቅረብ ወይም ማጠቃለል፣ ተማሪዎች ህጎችን በራሳቸው እንዲደርሱበት ከሚደረግ ዘዴ ያነሰ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ግን ለተማሪዎች ልምምድ ወይም ተግባር የበለጠ ጊዜ ይወስዳል፡፡

ስድስተኛው የልዩነት መሰረት የሆነው የተማሪዎች ተሳትፎ ነው (መሀመድና ሌሎች 2008)፡፡ በዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ማስተማር ተማሪዎች ትምህርታቸውን በንቃት እንዲከታተሉ ሲያግዝ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ማስተማር ሂደት ግን ተማሪዎች ትምህርታቸውን በንቃት ላይከታተሉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የመምህር ገለጻ የተማሪዎችን መስተጋብር

ስለሚቀንስ ነው፡፡ በሌላ መንገድ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ተማሪዎች ከተሳትፎ አልባ ወደ ተሳታፊነት ይሸጋገራሉ (ሻፈር፣ 1989)፡፡

እንደ መሀመድና ሌሎች (2008) ገለጻ ሰባተኛው ልዩነት ቀላል (easy) ወይም ተራና (simple) ከባድ (difficult) ወይም ውስብስብነት (complex) ነው፡፡ ፊሸር (1979)ን በመጥቀስ ባለሙያዎቹ እንደሚገልጹት ከዝርዝርር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ሰዋስው ማስተማር ለቁጥጥር ቀላልና ብቃት ያለው ሲሆን በተደጋጋሚ መገልገል ግን አሰልቺ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ መንገድ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ሰዎች ጠንክረው እንዲሰሩ የሚያደርግና ጊዜ የሚወስድ ለቁጥጥርም አቅም የሚጠይቅ ነው፡፡ የውጭ ቋንቋ ሰዋስው ህግ ከተወላጅ ቋንቋ (native language) ቀሎ የሚገኘው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ሲቀርብ ነው፡፡ ከተወላጅ ቋንቋ ጋር እኩል ወይም የበለጠ ውስብስብነት የሚኖረው ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ዘዴ ሲቀርብ ነው፡፡

## 2.6.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር በሚለው ነጥብ ላይ ጂያንግ (2012) እንደሚያስረዱት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው በማስተማር ሂደት፣ሁለቱን ዘዴዎች በአንድላይ በሰዋስው ትምህርት መተግበር ከሁለቱ አንዱን ብቻ ከመጠቀም ይበልጥ ውጤታማ ነው፡፡

ጂያንግ (2012) በቻይና አገር በእንግልዝኛ ቋንቋ ላይ ባደረጉት ጥናት የደረሱበትን ውጤት እንደሚከተለው አመልክተዋል፡፡ ጥናቱ በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ 70 ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ ሶስት የተለያዩ ሰዋስው ማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ውጤት በማወዳደር የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱ ላይ ተግባራዊ  የተደረጉ ዘዴዎችም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴና ሁለቱን ዘዴዎች መጠቀም ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የእያንዳንዱን ተማሪ ግላዊ ውጤት በሚያንጸባርቅ መልኩ በሙከራ ላይ የተመሰረተ ግላዊ ውጤት (based on self-reported reflection on experiment)፣ ተማሪዎችን በመማር ማስተማር ሂደት የተደረገ ምልከታና በቅድመና ድህረ ትምህርት ላይ የተመሰረተ ፈተና ውጤት ላይ ትንተና አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር ውጤት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ነጣጥሎ ሰዋስው ከማስተማር ውጤት በከፍተኛ ደረጃ በልጦ እንደተገኘ ያመለክታሉ፡፡

ዩኪ (2008) በጃፓን አገር ቶኪዮ አካባቢ በሚገኝ ሜትሮፖሊታን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 161 ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን በመጠቀም ጥናት አካሂደዋል፡፡ የዮኪ ጥናት ዋና ዓላማ አብዛኛውን ጊዜ በጃፓን እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የሚተላለፈው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ በመሆኑ ሁለቱን ዘዴዎች በመጠቀም ሰዋስው ማስተማር ያለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህም ሁለቱ ዘዴዎች ለተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ማስተማር ውጤታማ እንደሆኑ አመልክተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዘዴዎቹ የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎት ከፍ እንደሚያደርጉ በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

አብዶና ራማኒ (1990) በኦማን አገር ሱልታን ቃቦስ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሙያ ስልጠና የሚወስዱ ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው በማስተማርና ሁለቱን ዘዴዎች ለየብቻ ነጣጥሎ በሰዋስው ትምህርት መጠቀም ሂደት የትኛው ውጤታማ እንደሆነ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ሁለቱን ዘዴዎች ነጣጥሎ በሰዋስው ትምህርት ውስጥ መጠቀም በሰዋስው ትምህርት ውስጥ ሁለቱን ከመጠቀም የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

አዲአና (2012) በእንዶኔዥያ በእንግልዝኛ ቋንቋ የአንቀጽ ጊዜያት ላይ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን መጠቀም ያለውን አስተዋጽኦ በተመለከተ ጥናት አካሂደዋል፡፡ አዲአና እንደሚያስረዱት ማንኛውም የማስተማሪያ ዘዴ ሰዋስው በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጠንካራ ጎን (strengths) እንዳለው ሁሉ ደካማ ጎንም (weakness) እንዳለው ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ምክንያት መምህር የተለያዩ ማስተማሪያ ብልሀቶችን (strategy) ማሰብና ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህ በሚደረግበት ወቅት በመማር ማስተማር ሂደት ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ መርጦ ለተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እንደአስፈላጊነቱ ለመጠቀምና በተግባር ላይ ለማዋል ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት ይረዳል፡፡

ብሮውን (2007)ና ቶርንስበሪ (2002)ን በመጥቀስ አዲአና (2012) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎች ጠንካራ ጎንንና ደካማ ጎን እንደሚከተለው አመልክተዋል፡፡

ሰዋስው በማስተማር ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ያለው ጠንካራ ጎን፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ በቀጥታ ህጎችን የሚያቀርብ በመሆኑ ለተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ህግ በስፋት

ለመግለጽ ሰፊ ጊዜ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ መምህር ሰዋስዋዊ ህጎችን በስፋት ለማቅረብ እድል አለው፡፡ በተለይ ለወጣት (adult) የቋንቋ ተማሪዎች ብስለትና እውቀት እንዲጨብጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ህጎችን በመተንተን ቋንቋ ለመማር ለሚፈልጉ የቋንቋ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትኩረት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፡፡

ሰዋስው በማስተማር ሂደት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ያለው ደካማ ጎን፣ ይህ ዘዴ ለታዳጊ (young) ተማሪዎች አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ታዳጊዎቹ ረቂቅ የሰዋስው ትምህርት ሲቀርብላቸው ለመረዳት አቅም አይኖራቸውም፡፡ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ የሰዋስው ትምህርት ሲቀርብ የመማርያ ክፍሉን ድባብ መምህር ብቻ ስለሚቆጣጠር የተማሪዎችን የርስበርስ መስተጋብር ይቀንሳል፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የመምህር ገለጻ ከሌላው የመማሪያ ክፍል አያያዝ አኳያ ሲታይ እምብዛም የማስታወስ አጋጣሚ እንዲኖር አያደርግም፡፡

ሰዋስው በማስተማር ሂደት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ያለው ጠንካራ ጎን፣ ታዳጊ ተማሪዎች በተለይ ረቂቅ የሰዋስው ትምህርት ለመረዳት (abstract concept of grammar) አስቸጋሪ ለሚሆንባቸው፣ የተተኳሪውን ሰዋስው በንቃተ-አልባ እንዲማሩ ያግዛቸዋል፡፡ ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል፤ከዚህ በተጨማሪ ሰዋስው መማር ይበልጥ ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች በመማር ማስተማር የነቃተ-ተሳትፎ እንዲያደርጉና ትምህርታቸውንም በንቃት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፡፡

ሰዋስው በማስተማር ሂደት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ያለው ደካማ ጎን፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋስው ህግ በማስተማር ሂደት ጋር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ ሲነጻጸር ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡፡ ተማሪዎች በሚያጠፉት ረጅም ጊዜና ጉልበት የዋናውን ዘዴ ዓላማ ከሳቱ ተማሪዎቹ የተገበሩት ህጉን መተንተን እንጂ ትርጉምን መሰረት ያደረገ የሰዋስው ትምህርት አላገኙም ማለት ነው፡፡ተማሪዎች በራሳቸው የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋስው ህግ ከሚሰጡት ምሳሌ በመነሳት ሲፈልጉ የተሳሳተ ህግ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከሚጠበቀው ዓላማ በተለየ መልኩ እንዲጓዙ ያደርጋቸዋል፡፡ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ መማር የለመዱ ተማሪዎች የሚቀርብላቸው ትምህርት እንደጠበቁት ሳይሆን ሲቀር ለቀረበው ትምህርት ተነሳስኦ ላይኖራቸው ይችላል፡፡

አዲአና (2012) እንደሚያስረዱት የሁለቱን ዘዴዎች ጠንካራና ደካማ ጎን መሰረት በማድረግ ከሁለቱ ዘዴዎች አንዱን ከመጠቀም ሁለቱን መጠቀም የተሻለ ነው፡፡ ሁለቱን ዘዴዎች በመገልገል ከላይ የቀረበውን ጠንካራ ጎን ማሳደግ ይቻላል፡፡ ዘዴዎቹን በሰዋስው ትምህርት ሂደት በመጀመሪያ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ በመጠቀም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴን ደግሞ አስከትሎ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሁለቱን ዘዴዎች በዚህ መልኩ የመጠቀሙ ምክንያት የሚቀርበው ሰዋስው ትምህርት ትርጉም ያለው እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡ በተለይ ወጣት ተማሪዎች በረቀቀ መንገድ በማሰብ የተተኳሪውን ቋንቋ እውቀት እንዲያሳድጉ ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎች የተተኳሪውን ቋንቋ እውቀት ካፈሩ በኋላ የዝርዝር ዘዴ ህጉን በመረዳት በንግግር ውስጥ የመጠቀም ብቃታቸው እንዲያድግ ያግዛል፡፡

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሰዋስው ማስተማር በኑናን (2003) እንደተተገበረ አዲአና (2012) ገልጸዋል፡፡ ኑናን እንዳመለከቱት ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር በተለይ ለተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመራጭ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ተጠቅሞ የእንግልዝኛ ቋንቋ የአንቀጽ ጊዜያትን (English tenses) ማስተማር ለማስታወስ ወይም ለመረዳት ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ለተግባቦት እንዲጠቀሙም ያግዛቸዋል (አዲአና፣ 2012)፡፡

በተመሳሳይ ሀሳብ አዲአና (2012) በጥናታቸው እንዳመለከቱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው ለማስተማር መምህር ሲጠቀም መጀመሪያ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ ማቅረብ ከዚያም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴን መጠቀም፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴ የአንቀጽ ጊዜያትን ህግ እንዲያስታውሱ ሲያደርግ ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴ ደግሞ ተማሪዎች ህጎችን እንዲረዱና ለተግባቦት እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው የባለሙያዎች (አዲአና 2012፤ ጂያንግ 2012) ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ዘዴዎችን በሰዋስው ትምህርት ውስጥ መጠቀም ውጤታማ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን ዘዴዎቹን አስቀድሞ በመጠቀሙ ሂደት ወጥ የሆነ አቋም የያዙ አይመስልም፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ፍትነታዊ (Experimental) የምርምር ስልትን ተከትሎ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህ የምርምር ስልት መሰረትነት ቅድመ-ፍትነታዊ (pre-experimental) ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች የክፍል ደረጃውንና የጥናቱን አላማ መሰረት ያደረገ የሰዋስው ትምህርት ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ የተዘጋጀውን የትምህርት ይዘት ሳይማሩ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጧቸዋል፡፡

## 3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን በሻምቡ ከተማ በአቢሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት ለአጥኚዋ ቅርብ በመሆኑ ካላት የጊዜና ጉልበት ምክንያት በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ ለአጥኚዋ ቅርብ በመሆኑ የምርምሩን ሂደት በቅርበት ለመከታተል አመቺ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ እንዲካተት በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡

በጥናቱ የተሳተፉት በ2015 ዓ.ም በሻምቡ አብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ደረጃ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በነዚህ ክፍሎች ወንድ 222 ሴት 291 በአጠቃላይ 513 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ ከነዚህ በሁለት ክፍል ተማሪዎችን በመመደብ በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች የእድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም 30 ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ተመርጠዋል፡፡ ተማሪዎቹ የተማሪዎችን ቁጥር በዚህ መወሰን ያስፈለገው ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አስተማማኝነቱንና ተገቢነቱን ለመጠበቅ ታስቦ ነው፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ የጥናቱን ንድፍ መሰረት በማድረግ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.2.1. ፈተና

በዚህ ጥናት በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገለው ፈተና ነው፡፡ በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች አንድ ፈተና በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መሰረት አድርጎ በአጥኚዋ ተዘጋጅቷል፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተና አላማ ተደርጎ የተዘጋጀው የጥናቱ ተሳታፊዎች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የተማሪዎችን ሰዋስው ዳራዊ እውቀት ለመፈተሽ ነው፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን አራት ክፍሎች ያሉት 20 ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 10 የምርጫ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ይህም የቃል ክፍሎችን የመለየት አቅም ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ሶስት ክፍት ቦታን ማሟላት  የሚጠይቁ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ዓረፍተ ነገርንና ዓረፍተ ነገር በውስጡ ከሚይዛቸው ዋና ተዋቃሪ አካላት ሁለቱን (ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ) የመለየት አቅም የሚለኩ ናቸው፡፡ ሶስተኛው ክፍል አምስት የአዛምድ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ጥያቄዎቹም የቃል ክፍሎችን በተገቢው ቦታ የማስገባት ችሎታን መለካት መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ አራተኛው ክፍል ሁለት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተ ነገር መገንባትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ፈተናው ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት አስተማማኝነቱን ለመጠበቅ የአጥኚዋ አማካሪና ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን እንዲገመግሙት ተደርጓል፡፡ ፈተናው ከተገመገመ በኋላ በጥናቱ ከሚሳተፉ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ባላቸው 10 ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የሙከራው ፈተና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሞ በአራሚ ዘለል የአስተማማኝነት መገመቻ ቀመር ተሰልቶ አስተማማኝነቱ 0.92 ሁኗል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የተገኘው ውጤት ለዋናው ጥናት መሰረት የጣለ ሲሆን ፈተናውን ከገመገሙት መምህራን የተገኘውን የግምገማ ውጤት መሰረት በማድረግ ማስተካከያ በማከል ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ፈተናውን የፈተነችው አጥኚዋ ስትሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች ለፈተና አመቺ በሆነ አቀማመጥ ተቀምጠው ፈተናውን ተፈትነዋል፡፡ ፈተናው በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካይነት እንደየ ጥያቄዎቹ ባህርይ የጋራ መስፈርት በማውጣት ታርሟል፡፡ በአራሚዎች መካከል ያለው ስምምነት በኣራሚ ዘለል የአስተማማኝነት መገመቻ ተሰልቷል፡፡ ይህ ውጤት በአራሚዎች መካከል ከፍተኛ ስምምነት እንዳለ ያመለከተ በመሆኑ ሁለቱ አራሚዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ

የሰጡት ውጤት ከተደመረ በኋላ ለሁለት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ውጤት የጥናቱ ተሳታፊዎች ውጤት ተደርጎ ተመዝግቧል፡፡

ከቅድመ ትምህርት ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በተጨማሪ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ድህረ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተና ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተና ዓላማ ተደርጎ የተዘጋጀው ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስው የማስተማሪያ ዘዴዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ለስድስት ሳምንት ከተማሩ በኋላ ዘዴዎቹ በተማሪዎች የሰዋስው እውቀት ላይ ያላቸውን ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡ የፈተናው አስተራረምና አመዘጋገብ እንደ ቅድመ ትምህርት ፈተናው ሲሆን በዚህ ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የተገኘው ውጤትም ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና አንጻር የጎላ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

### 3.2.2. የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቁ ዋና አላማ በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎች ሰዋስውን መማር/ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማወቅ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ባለአራት ስኬል ስምምነት መገለጫዎች እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ ጥያቄዎቹም በድርድር የጥያቄ አቀራረብ (Matrix questions) ቀርበዋል፡፡

መጠይቁ ሀይለማሪያም (2011) በርገስና ኤቴሪግተን (2002)ን ጠቅሶ በጥናቱ የተጠቀመበትን ለጥናቱ እንዲስማማ ማሻሻያ ተደርጎበት 15 ጥያቄዎችን እንዲይዝ ተደርጎ በአጥኚዋ የተዘጋጀ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በጥናቱ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በአጥኚዋ አማካሪ እንዲሁም በቋንቋና በስነልቦና መምህራን ተገምግሞ በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በመጠይቁ የተካተቱ ጥያቄዎች አራት የመልስ መስጫ መወሰኛ አማራጮችን የያዙ ሲሆን ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ በጣም እስማማለሁ (4)፣ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2)ና በጭራሽ አልስማማም (1) የሚሉ ናቸው፡፡ በመጠይቁ አሞላል ሂደት በመጠይቁ ላይ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት በትክክል ያልተሞላ ካለ ማጣራት ተደርጎበት ትንታኔ ተካሂዶበታል፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያለው የጽሁፍ መጠይቅ በተማሪዎች እንዲሞላ የተደረገው፣ በቅድመ ትምህርትና ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ነው፡፡ በቅድመ ትምህርት መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገበት ምክንያት

ተማሪዎች በዘዴዎቹ ላይ ከመነሻው የነበራቸውን ፍላጎት ለማወቅ ነው፡፡ በድህረ ትምህርት መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገበት ምክንያት ተማሪዎች በተጠቀሱት ዘዴዎች ሰዋስውን መማር/ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ ነው፡፡ በመጠይቁ አሞላል ሂደት በመጠይቁ ላይ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት በትክክል ያልተሞላ ካለ ማጣራት ተደርጎበት በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፍላጎት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥም በመጠይቁ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ትንታኔ ተካሂዶበታል፡፡

## 3.3. የጥናቱ ሂደት

ከተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለጥናቱ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ አካላት የምርምሩን አላማ በማስረዳት ይሁንታቸውን በማግኘት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጥኚዋ የክፍል ደረጃውን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን የትምህርት ይዘት ከመማራቸው በፊት ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፤ እንዲሁም ቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ሞልተዋል፡፡ ቅድመ ትምህርት ፈተናውን ከተፈተኑና የጽሁፍ መጠይቁን ከሞሉ በኋላ ወደ ትምህርት ተገብቷል፡፡ ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ከግምት በማስገባት ለክፍል ደረጃው ከቀረበው መማሪያ መጽሐፍ ላይ በመመስረት የቀረበውን የትምህርት ይዘት የሚያጎለብቱ ሀሳቦችንና የማስተማሪያ ሂደቶችን የመስኩ ባለሙያዎች ካቀረቧቸው መጻህፍት የተገኘውን ሀሳብ ከግምት በማስገባት በአጥኚዋ በተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሐፍ ለስድስት ሳምንት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ከትምህርት ፈረቃቸው ውጭ በመገኘት በሳምንት ሁለት ጊዜ ማክሰኞና ሀሙስ በቀን ለአንድ ሰዓት ትምህርቱን እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ ተሳታፊዎች ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለፈተናው የተሰጠ ጊዜ አንድ ሰዓት ሲሆን ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተና ወረቀታቸው በአጥኚዋ ተሰብስቦ ፈተናውን እንዲያርሙ ለተመረጡ መምህራን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከድህረ ትምህርት ፈተናው በማስከተል የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የተሞላውንም የጽሁፍ መጠይቅ በአግባቡ በማደራጀት ትንታኔ እንዲካሄድበት ተደርጓል፡፡

### 3.4. የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት

አጥኚዋ ለክፍል ደረጃው ከቀረበው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ተመስርታ የቃል ክፍሎችን እንዲሁም ዓረፍተ ነገርን ለትምህርት ይዘትነት በመምረጥ ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎች አቅርቧል፡፡

የመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅቱን በተመለከተ አንድ ቃል በስም፣ በቅጽል፣ በግስ፣ በተውሳከግስና በመስተዋድድ የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበትን መስፈርትና እንዲሁም ዓረፍተ ነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ የዓረፍተ ነገር ዋና ተዋቃሪ አካላት ምንና ምን እንደሆኑ ቀርቧል፡፡ የቀረቡትን ይዘቶች በተመለከተ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው ምሳሌዎች በመነሳት የተለያዩ ምሳሌዎችን ለቃል ክፍሎችና ዓረፍ ተነገር በመስጠት የቃል ክፍሎችንና ዓረፍተ ነገርን በራሳቸው እንዲለዩና መምህሩም ተጨማሪ ማብራሪያዎችን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ዝግጅትም የሚከተሉትን ሀሳቦች ከግምት ያስገባ ነው፡፡

1. ለቃል ክፍሎች ምሳሌዎችን በመስጠት ከምሳሌዎቹ በመነሳት ተማሪዎች የራሳቸውን ምሳሌዎች በመስጠት የቃል ክፍሎችን እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ ዓረፍተ ነገርን በተመለከተ ስለ አረፍተ ነገር ምንነት ገለጻ ከተሰጣቸው በኋላ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች ከምሳሌው በመነሳት ሌሎች ምሳሌዎችን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ተዘበራርቀው የተሰጡትን ቃላት አስተካክለው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱም ተደርጓል፡፡
2. ከዝርዝር ወደ ጥቅል ዘዴ ትምህርቱ ሲቀርብ ለተማሪዎች ልምምድ የተመደበው ሰዓት ለመምህሩ ንግግር ከተመደበው ሰዓት እንዲበልጥ ተደርጓል፡፡ ይህ የሚሆንበትም ምክንያት ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ሰዋስዋዊ ህግጋት ለራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከጥቅል ወደ ዝርዝር አቀራረብ በሚቀርቡ ይዘቶች ላይ መምህሩ ሰፊውን ጊዜ እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡
3. ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቡድንና ጥንድ ጥንድ በመሆን ይለማመዳሉ፤መምህሩም በቀረቡት ይዘቶች ላይ ገለጻ ተደርጓል፡፡
4. መምህሩና ተማሪዎች የሚቀርበውን ትምህርት ሂደት በተፈለገው መጠን እንዲቀርብ ለማስቻል ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተግባር ፈጽመዋል፡፡

### 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ተፈላጊው መረጃ ከተሳታፊዎች በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰበ በኋላ በስርዓት ተደራጅቷል፡፡ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በስርአት ከተደራጀ በኋላ በሁለቱ አማካይ ውጤት ልዩነት ይኖረው እንደሆነ ለማረጋገጥ ውጤቱ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት (Repeated Measure sample t-test) ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡ በዚህም መሰረት በፈተና የተገኘው የተማሪዎች ውጤት የነጻነት ደረጃውንና የጉልህነት ደረጃውን እንዲሁም የቲ-ዋጋን ጨምሮ የተገኘው ውጤት በማወዳደር የተደረሰበት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡ ለምናልባት ስህተት ከፍና ዝቅ ተብሎ P= 0.05 ተወስዷል፡፡

ከፈተና በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ከተሞላ በኋላ በስርአት ተደራጅቷል፡፡ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በስርአት ከተደራጀ በኋላ በሁለቱ አማካይ ውጤት ልዩነት ይኖረው እንደሆነ ለማረጋገጥ ውጤቱ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት (Repeated Measure sample t-test) በማስላት ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው የተማሪዎች ምላሽ የነጻነት ደረጃውንና የጉልህነት ደረጃውን ጨምሮ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በምርምሩ ሂደት በተሰጡ ቅድመ ሙከራና ድህረ ሙከራ ፈተናዎች እንዲሁም በምልከታ የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

## 4.1.የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት አላማ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ አቀራረብ ሲማሩ የሚያሳዩትን ለውጥ መፈተሽ ሲሆን በድህረ ሙከራ ፈተናና በቅድመ ሙከራ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል የታየው ልዩነት በሰንጠረዥ አንድ ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዝ 1፤ በቅድመ ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት

| የሰዋስው ትምህርት ውጤት | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | df |
|---|---|---|---|---|
| ድህረ ሙከራ | 30 | 30.77 | 7.079 | 29 |
| ቅድመ ሙከራ | 30 | 23.53 | 8.701 | |

በሰንጠረዥ 1 እንደተመለከተው የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት (Repeated Measure Sample t-test ) ስሌት እንደሚያሳየው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ አቀራረብ ትምህርት አማርኛን የሚማሩ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመና የድህረ ፈተናዎች አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ጥናቱ ያሳያል ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛን የቃል ክፍሎችንና ዓረፍተ ነገርን በዘዴዎቹ ከመማራቸው በፊት በሰዋስው ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (23.53) በዚህ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት (30.77) አንሶ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተሳታፊዎቹ በዘዴዎቹ መማራቸው በውጤታቸው ላይ ለውጥ እንዳስከተለ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በቅድመ ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች በተሰበሰበው

መረጃ መሰረት መጀመሪያ ምላሽ የተሰጠው የምርምር ጥያቄ ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሰዋስውን የማስተማር አቀራረብ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ተጽዕኖ መፈተሽ የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ጥንድ ናሙና t- ቴስት ተግባራዊ ተደርጎ ውጤቱ በሰንጠረዥ 2 ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 2 ፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር በጥንድ ናሙና t- ቴስት (paired sample t-test) ፍተሻ

| ተላውጦ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የt-ዋጋ | t-cri |
|---|---|---|---|---|
| የሰዋስው ችሎታ | 7.233 | 3.636 | 16.11 | 2.045 |

የነጻነት ደረጃ (df) 29፣ *p< 0.05

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ውጤት ላይ አወንታዊ ተጽእኖ እንዳለው ሰንጠረዥ 2 ያሳያል፡፡ በቅድመ ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች የተሰበሰበው ውጤት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ አማካይ ውጤቱ 7.233 ሁኗል፡፡ በ29 የነጻነት ደረጃና በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ 5% የምናልባት የስህተት ይሁንታ በመተውና 95% እርግጠኛ በመሆን በቲ- ሰንጠረዥ ላይ ከተመለከተው የtcr ዋጋ 2.045 ጋር ሲነጻጸር የቲ-ዋጋ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት እንደተቻለው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር አማርኛ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎች በጎ ተጽእኖ እንዳለው አመላክቷል፡፡ የአማርኛን የቃል ክፍሎችና ዓረፍተ ነገርን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከመማራቸው በፊት በተፈተኑት የሰዋስው ፈተናና በዚህ አቀራረብ ተምረው በተፈተኑት የድህረ ሙከራ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት ተስተውሏል፡፡ በዚህም በድህረ ሙከራ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት በቅድመ ሙከራ ካስመዘገቡት ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ በሰንጠረዥ 2. እንደተመለከተው በተሰላው ስሌት መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ

ሙከራና በድህረ ሙከራ ፈተና ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ (0.914) በጣም ከፍተኛ ሲሆን ግንኙነታቸውም አወንታዊ ነው፡፡ ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው በቅድመ ሙከራ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በድህረ ሙከራ ፈተናም ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ወይም በቅድመ ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በድህረ ፈተናም ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል ወደ ሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ይመስላል፡፡

በጥናቱ ሊመለስ የተፈለገው ሁለተኛው ጥያቄ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድን ነው? የሚለው ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ተግባራዊ የተደረገው የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁም እንዲሞላ የተደረገው በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ሂደት ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የሞሉት መጠይቅ ውጤት በገላጭ ስታቲስቲክና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም ከታች በሰንጠረዥ 3 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 3 . የተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት

(Repeated Measure sample t-test)

| ውጤት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ(ባለሁለት ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ፍላጎት | 30 | 37.05 | 2.83 | 6.651* | 29 | 0.001 |
| የድህረ ፍላጎት | | 42.40 | 2.82 | | | |

*$p < 0.05$

በሰንጠረዥ 3. እንደ ተመለከተው የድህረ ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (42.40) ከቅድመ ፍላጎት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (37.05) የሚበልጥ ይመስላል፡፡ መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የድህረ ፍላጎት መደበኛ ልይይት ከቅድመ ፍላጎት መደበኛ ልይይት ያነሰ መሆኑን የሰንጠረዡ መረጃ ያሳያል፡፡

በሰንጠረዥ 3. የተመለከተውን በቅድመ ፍላጎትና ድህረ ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ ደግሞ የዳግም ልኬት ናሙና ቲ-

ቴስት (Repeated sample t-test) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በድህረ ትምህርትና በቅድመ ትምህርት አማካዮች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ (t (29) = 6.65፣ p<0.05) መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ ይህም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰዋስው ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ እንዳለው ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታ በማጎልበት ረገድ የላቀ ሚና አለው፡፡ በዚህ መሰረት በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ በተጨማሪም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰዋስው ማስተማር ሰዋስው በመማር ፍላጎት ላይ አስተዋጽኦ እንዳለው የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ በዚህም በቅድመ ፍላጎትና ድህረ ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡

### 4.2.የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም ትንተና ይረዳ ዘንድ ገላጭ ስታቲስቲክስና ዳግም ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ (Repeated sample t-test) ተደርጓል፡፡ በተደረገው ትንተና የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህ ውጤት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ዕውቀት ያጎለብታል የሚል አንድምታ አለው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ተሳታፊዎች የአማርኛ ቋንቋ የቃል ክፍሎችንና ዐረፍተ ነገርን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ መማራቸው የሰዋስው ፈተና ውጤታቸውን እንዳሻሻለውና በተማሪዎች መካከልም የችሎታ መቀራረብ እንደፈጠረ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎትና የሰዋስው ችሎታ ማጎልበቱን ያመላከተው የዚህ ጥናት ውጤት የተማሪዎችን ሰዋስው እውቀት ለማጎልበት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ማስተማር

ውጤታማ ያደርጋል፤ ከሚለው ማክብልቸር (2006)፣ ብሮውን (1994፣2000)፣ ኤሚሊ (2009) አብርሃም (1985)፣ ሮዛና ኦኔል (1999)ና ሻፌር (1989)ን ጠቅሰው ካቀረቡት፣ ሮጀር ክሎው (ዓ/የ)ን ጠቅሰው ከገለጹት ፣አዲአና (2012)፣ ዮኪ (2008)፣ ጂያንግ (2012) ሀሳብና የጥናት ውጤቶች ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡ በሌላ በኩል ግን አብዶና ራማኒፔሩር (1990) ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው ከማስተማር ዘዴዎቹን ለየብቻ ነጣጥሎ ሰዋስው ማስተማር ውጤታማ ያደርጋል፤ የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱትን የዚህ ጥናት ውጤት አልደገፈውም፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛው ዓላማ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስው ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስው መማር ፍላጎት ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቅድመ ፍላጎትና በድህረ ፍላጎት የመጠይቅ ምላሽ መካከል ጉልህ ልዩነት የታየ ሲሆን የድህረ ትምህርት ፍላጎት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፍላጎት አማካይ ውጤት ልቆ ተገኝቷል፡፡ ይህም ውጤት ዮኪ (2008) ሁለቱን ዘዴዎች በሰዋስው ትምህርት ውስጥ መጠቀም የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት ከማጎልበት አንጻር ከፍተኛ ድርሻ አለው፤ በማለት ከደረሱበት ማጠቃለያ ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡

ሁለቱን አቀራረቦች ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታ ለማሳደግና ሰዋስው የመማር ፍላጎት ለማጎልበት ትልቅ አስተዋጽዖ አለው በሚል ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎትና የሰዋስው ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ለማስተማሪያነት የቀረቡ መጽሐፎች ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እድል የሰጡ በመሆኑ ነው፤ የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ዕውቀት ያጎለብታል የሚል አንድምታ አለው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት ያለው ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ዘዴዎቹ የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ላላቸው ሚና ተጨማሪ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎች ሰዋስው እውቀት በመጎልበቱ ለተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት መጎልበት አስተዋጽዖ አድርጓል ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀትና ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሊመለሱ የታሰቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና ምንድን ነው?
2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

ከላይ ለቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች አስተማማኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውለዋል፡፡ በጥናቱ የተሳተፉት በ2015 ዓ.ም በሻምቡ አብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ደረጃ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቱ ስድስት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በነዚህ ክፍሎች ወንድ 222 ሴት 291 በአጠቃላይ 513 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ ከነዚህ በሁለት ክፍል ተማሪዎችን በመመደብ ጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ተማሪዎች የእድል ሰጭ የንሞና ዘዴን በመጠቀም 30 ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ተመርጠዋል፡፡ የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

ተሳታፊዎችም መርሀ ትምህርቱንና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፋቸውን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን መጸሐፍ ከመማራቸው በፊት የቅድመ ትምህርት ፈተና በጥናቱ አማካሪና በሌሎች ባለሙያዎች ማስተካከያ ታክሎበት፣ በሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ የተማሪዎቹን የሰዋስው ዳራዊ ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ቀጥሎም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን መጸሐፎች ለስድስት ሳምንት ተምረዋል፤ በመጨረሻም

ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰባስቧል፡፡

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት ማጎልበቱንና አለማጎልበቱን ለመረዳት የፅሁፍ መጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በመጠይቁ 15 ጥያቄዎች የተካተቱበት ሲሆን ሀይለማሪያም (2011) በጥናቱ በርገስና ኤቴሪግተን (2002)ን ጠቅሶ የተጠቀመበትን ሁለቱን ዘዴዎች እንዲያካትት በማድረግና ለጥናቱ በሚመች መልኩ በማሻሻል በዘዴዎቹ ላይ ያላቸውን ፍላጎት እንዲለካ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታቲስክስ ተተንትነዋል፡፡

በፈተና አማካይነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ ($p<0.05$) ጉልህ ልዩነት በመታየቱ በዘዴዎቹ ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታን እንደሚያጎለብት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የታየው መሪ ጥያቄ ዘዴዎቹን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር በተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድን ነው? የሚል ነበር፡፡ በቅደመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የፍላጎት መረጃ መሰረት በተሳታፊዎች የቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፍላጎት አማካዩች መካከል በስታቲስቲክስ ($p<0.05$) ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ በዚህም ዘዴዎቹን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር በሰዋስው መማር ፍላጎት ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 5.2. መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ተደርሷል፡፡

1. በጥናቱ ውጤት መሰረት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታ በማጎልበት ረገድ

አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ ይህም ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታ በማጎልበት ረገድ ትልቅ ሚና አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡

2. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ሰዋስው በማስተማርና በተማሪዎች ሰዋስው የመማር ፍላጎት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ፡፡ ይህም ዘዴዎቹን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው የመማር ፍላጎት በማጎልበት ረገድ አስተዋጽዖ እንዳለው ያሳያል፡፡

## 5.3. አስተያየት

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ግኝቶችና ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የሚከተሉት መፍትሄዎች ተጠቁመዋል፡፡

1. ጥናቱ ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰዋስው በማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው ችሎታ ማጎልበት እንደሚቻል አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መጻህፍት ሲዘጋጁ ሁለቱን ዘዴዎች ባማከለ ሁኔታ የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ ለማጎልበት የሚረዱ መልመጃዎችና ተግባራት ያካተቱ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡
2. የቋንቋ መምህራን ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅመው በመጠቀም የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ የሚያጎለብቱ መልመጃዎችንና ተግባራትን ተጠቅመው ሰዋስው ቢያስተምሩ የተሻለ ይሆናል፡፡
3. መምህራንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ተማሪዎች የሰዋስው ዕውቀታቸውን ለማሳደግ ሁለቱን ዘዴዎች ተጠቅመው በቀረበ የሰዋስው ትምህርት እንዲጋለጡ ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ ተመራጭነት አለው፡፡
4. በዘርፉ ጥናት የሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን ጨምሮ ሌሎች የሰዋስው ማስተማርያ ዘዴዎች ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢያካሂዱ የተማሪዎች የሰዋስው ችሎታና ሰዋስው የመማር ፍላጎት ሊጎለብት ይችላል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ማረው ዓለሙ፡፡ (1998 ዓ.ም)፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማረው ዓለሙ፡፡ ( 2003ዓ.ም)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*፡፡ (2nd ed.)፡፡ አዲስ አበባ፤ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባዬ ይማም፡፡ (1987)፡፡ **ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Abreham Degu(2008). *The Effectiveness ofthe Teaching of English Grammar as a Foreign Language throughthe Integration of Form, Meaning and Use.* Unpublished MA Thesis.Addis Ababa University.

Adi ana, R. ( 2012). Teaching English Tenses to EFL Learners: Deductive or Inductive?. Bali- Indonesia: Ganesha University. *International Journal for Cross-Disciplinary Subjects in Education (IJCDSE), Special Issue* Volume 2 Issue 2, 2012 infonimics- society.org.

Al Ghazali, F. (2006). *The Presentation- Practice- Production Vs Consciousness-Raising:*Which Is Efficient in Teaching Grammar?The University of Birmingham Unpublished.

Batstone, R. (1994). *Grammar.* Oxford: Oxford University Press.

Chan, T.P. (2004). "*The effect of CALL Approaches on ELF College studentes' Learning of Verb-noun Collocation*." Unpublished MA Thesis, National Tsing Hua University.

Chomsky, N. (1977). *Essays on Form and Interpretation.* New York: North Holland.

Elis (2006). *Current issues in the teaching of grammar:* An SLA perspective. TESOL Quarterly 40, 1, 83—107

Fischer, A. R. (1979). "*The inductive-deductive controversy." revised*. Modern Language Journal, 63(3), 98-105.

Halliday, M. (2004).*An Introduction to Functional Grammar*. London: Edward Arnold.

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar*. London: Longman Publisher

Krashen.S. (1982). *Principles and practice in second language acquisition*. Englewood Cliffs, NJ: Prentice-Hall

Lightbown, M. and Spada, Nina(2006).*How Languages Are Learned*. (3rd Edition). China: Oxford University Press.

Mckay, S. (1987). *Teaching Grammar, Form, Function and Technique.* New York: Prentice Hall.

Mohammed and Etal. (2008). The Effects of Deductive and Inductive Approaches of Teaching on Jordanian University Students' Use of The Active and Passive Voice in English: college Student Journal, 01463934, Jun2008 part B, Vol. 42, Issue 2.

Mellese Gelaneh (2008). *Amharic Second Language Teachers Pedagogical GrammarApproaches*. The Case of Oromia. Unpublished MA Thesis.Addis Ababa University.

Richards, C. and Schmidt. (2002). *Longman Dictionary of LanguageTeaching and Applied Linguistics* (3rded.) Pearson Education Ltd.

Rutherford, W. (1987). *Second Language Grammar Learning and Teaching.*London, New York: Longman.

Simin, C. (2013). The Effect Of Inductive vs Deductive Instractional Approach In Grammar Learning Of ESL Learners: vol.2(2). Irans. www.iresearcher.org

Thornsbury, S. (1999). *How to Teach Grammar*. Longman: Person Edition. Ltd.

Wang, L. Y.(2002). *Effects of Inductiva and deductive approachs on EFL Learning Collocation Patterns. Taiwan:* Yunlin University of science and Technolagy, Douliou.

Widdowson, H. (1978).*Teaching Language as a Communucation*. Oxford: Oxford University Press.

Wilkins, D. (1976) *Notional syllabuses*. Oxford: Oxford University Press.

Yuki, M. (2008). The Effectiveness of Learner-centered Grammar Teaching:

*Journal Of foreign language education.*Vol.5,p.115-143. http://koara.lib.keio.ac

# አባሪ 1

# ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ የቃል ክፍሎችን ለማስተማር የቀረበ መጽሐፍ

ይህ የመማር/ማስተማሪያ መጽሐፍ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍና መርሀ ትምህርት መሰረት በማድረግ ነው የተዘጋጀው፡፡ የቃል ክፍሎችን እንዲሁም ዓረፍተ ነገርን በትምህርት ይዘትነት በመምረጥ ትምህርቱ የቀረበ ሲሆን ለተመረጡ የትምህርት ይዘቶች ማለትም የቃል ክፍሎችና ዓረፍተ ነገር ተማሪዎች ከኣካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የተለያዩ ምሳሌዎችን እንዲያቀርቡ በማድረግና ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት የቀረበ ነው፡፡

መምህር፡- አጥኚዋ

ትምህርት የሚሰጥባቸው ቀናት፡- ማክሰኞና ሀሙስ (በቀን ለአንድ ሰዓት)

የመማሪያ ክፍል፡- የኬሚስትሪ ትምህርት ሙከራ ክፍል

ጠቅላላ የትምህርት ሰዓት፡-12፡00

የትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከቀረበላቸውና ለራሳቸው ከሰጡት ምሳሌዎች በመነሳት የቃል ክፍሎችን ምንነትና ተግባር ይገልጻሉ፡፡
- ከመምህሩ ጋር በሚያደርጉት ምልልስና ርስበራሳቸው ከሚያደርጉት ንግግር በመነሳት የዓረፍተ ነገር ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- በራሳቸው ከሚሰጡት ምሳሌና ከመምህሩ በሚሰጣቸው ምሳሌና ገለጻ የዓረፍተ ነገር መሰረታዊ ክፍሎችን ለይተው ያመለክታሉ፡፡
- ከሚቀርብላቸው ምሳሌ በመነሳት ለራሳቸው አረፍተ ነገር በመገንባት ያመለክታሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ፤ ስም

በዚህ ክፍለ ትምህርት የስም ምንነት፣ አንድ በስም የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበት መስፈርት ይቀርብበታል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ 2፡00**

ከተማሪዎች መካከል አምስት ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት በሚከተለው መልኩ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ስሞችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ የተጠያቂዎችን ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ከተማሪዎቹ የተገኘውን ምላሽ በመዘርዘር ስሞችን ማለማመድ ይቻላል፡፡

መምህር፤(የቤተልሄምን ስም በመጥራት) የምታደንቂያቸውን አትሌቶች ስም ጥቀሺ

ቤቴልሄም፤ ሀይሌ          መሰረት

ቀነኒሳ          ጥሩነሽ

ደራርቱ

መምህር፤( የምስጋናን ስም በመጥራት) ከቤት እቃዎች አምስቱን ጥቀስ

ምስጋና፤ ወንበር          አልጋ

ብርጭቆ          ጠርሙስ

ኩባያ

መምህር፤( የአመንሲስን ስም በመጥራት) ከቤት እንስሳት አምስቱን ጥቀስ

አመንሲስ፤ በግ    በሬ

ፍየል    ፈረስ

ዶሮ

መምህር፤( የብስራትን ስም በመጥራት ) በእጅ ሊዳሰሱ በዐይን ሊታዩ ከማይችሉ ነገሮች አምስቱን ጥቀስ

ብስራት፤    ጨለማ          አየር          ልጅነት

ብርሃን          ደግነት

መምህር፤( የበረከትን ስም በመጥራት ) ለተለያዩ ነገሮች በጋራ መጠሪያነት ከሚያገለግሉ አምስቱን ጥቀስ

በረከት፤ ህዝብ አራዊት

ሰው እንስሳት

ሰራዊት

በተማሪዎቹ የተዘረዘሩት ቃላት ተግባራቸው ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ማድረግና ማለማመድ ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች ከላይ የተዘረዘሩት ቃላት ለነገሮች መጠሪያ ሆነው እንደሚያገለግሉ ከቀረበው ልምምድ እንዲገነዘቡ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ተግባር ሁለት**

ሁለት ተማሪዎችን በፍቃደኝነት በማስነሳት አንድ ምሳሌ /ፈረስ፣ ፈረሶች፣ ፈረስ-ኦች/ በመስጠት የሚከተሉት ቃላት ሲበዙ የሚኖራቸውን ቅርጽ ማለማመድ ይቻላል፡፡ ከተማሪዎች የሚገኘውን ምላሽ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በሚከተለው መልኩ በመጻፍ ማመልከት፣

| የተማሪ ስም | ቃል | ቃሉ ወደብዙ ቁጥር ሲቀየር የሚኖረው ቅርጽ |
|---|---|---|
| ነኢማ | በግ<br>በሬ | በጎች(በግ-ኦች)<br>በሬ (በሬ-ዎች) |
| ገመቺስ | ወንበር<br>ዶሮ | (ወንበር-ኦች)<br>(ዶሮ-ዎች) |

አሁንም እነዚሁ ተማሪዎች አንድ ነገር የራሳቸው መሆኑን ሲናገሩ ቃላቱ የሚኖራቸውን ቅርጽ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ በማመልከት ማለማመድ ይቻላል፡፡

| የተማሪ ስም | ቃል | ቃሉ ወደባለንብረት አመልካችነት ሲቀየር የሚኖረው ቅርጽ |
|---|---|---|
| ነኢማ | ውሻ<br>ደብተር | ውሻዬ (ውሻ-ዬ)<br>ደብተሬ (ደብተር-ኤ) |
| ገመቺስ | ቤት<br>ጎጆ | ቤቴ (ቤት-ኤ)<br>ጎጆዬ (ጎጆ-ዬ) |

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ አንድ የሚታወቅ ነገር ሲጠሩ የሚኖራቸውን ቅርጽ አንድ ምሳሌ/ ደብተር ፣ደብተሩ፣ደብተር-ኡ /በመስጠት ተማሪዎቹ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ እንዲናገሩ በማድረግ ማለማመድ

| የተማሪ ስም | ቃል | ቃሉ ወደዕውቅ አመልካችነት ሲቀየር የሚኖረው ቅርጽ |
|---|---|---|
| ነኢማ | በግ<br>በሬ | በጉ (በግ-ኡ)<br>በሬው (በሬ-ው) |
| ገመቺስ | ወንበር<br>ዶሮ | ወንበር (ወንበሩ-ኡ)<br>ዶሮው (ዶሮው-ው) |

በመጨረሻም ተማሪዎቹ መምህሩ ለሚከቱሉት ሀሳቦች ገለጻ በማድረግ አንድ ቃል በስም የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበትን መስፈርት በመዘርዘር ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

አንድ ቃል በስም የቃል ክፍል ለመመደብ፣

- ኦች/ዎች አብዢ ቅጥያ ምዕላዶችን የሚያስጠጋ ከሆነ
- ባለንብረት አመልካች ቅጥያ (-ኤ) ቅጥያ ምእላድ የሚያስጠጋ ከሆነ
- እውቅ አመልካች ቅጥያ ምእላድ(-ኡ) የሚያስጠጋ ከሆነ
- ለነገሮች መጠሪያ በመሆን የሚያገለግል ወዘተ

እነዚህን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚያሟላ ቃል በስም የቃል ክፍል ሊመደብ እንደሚችል በማስገንዘብ ትምህርቱን ማጠቃለል ይቻላል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በአናባቢ ሆሄ የማይጨርሱ ስሞች ቅጥያ ምዕላድ ሲያስጠጉ -ኦች/-ኤ ቅርጽ ሲይዙ፣ በአናባቢ ሆሄ የሚጨርሱ ስሞች ቅጥያ ምዕላድ ሲያስጠጉ -ዎች/ዬ ቅርጽ ይይዛሉ ለነዚህ የተለያዩ ምሳሌዎች በመስጠት እንዲገነዘቡ በማድረግ ትምህርቱን ማጠቃለል ይቻላል፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፤ ግስ

በዚህ ክፍል የግስ ምንነት፣ የግስ ተግባርና አንድ ቃል ግስ ለመባል የሚያሟላውን መስፈርት የሚቀርብበት ነው፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበ ጊዜ 2:00**

**ተግባር አንድ**

አንድ ወንድ ተማሪና አንድ ሴት ተማሪ በማስነሳት አጭር ድራማዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ በማድረግ ግስን ማለማመድ ይቻላል፡፡ ድራማዊ እንቅስቃሴውም ዳንኤል ምሳውን ሲበላ የሚያመለክትና ሰይዳ ዳንኤል በርትቶ እንዲያጠና ስትመክረው የሚያመለክት እንዲሆን ማድረግ፣ ከዚያም ሁለቱ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሌላ አንድ ተማሪ በማስነሳት “ዳንኤል ምን አደረገ? ” ብሎ ተማሪዎችን እንዲጠይቅ በማድረግ ከተማሪዎቹ የሚገኘውን መልስ መምህሩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ማመልከት፣ ከዚያም ተማሪዎች በግስ የቃል ክፍል የሚመደበውን ከስሩ በማስመር እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከተማሪዎች የተገኘው መልስ የሚከተለውን እንደሚመስል መከታተል ያስፈልጋል፡፡

ዳንኤል እጁን ታጠበ።

ዳንኤል ምሳውን በላ።

ተማሪው ሰይዳ ምን እያደረገች እንደ ነበር እንዲጠይቃት ማዘዝ፣ ከተማሪዋ የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ግስን ማለማመድ ይቻላል። ከተማሪዋ የተገኘው መልስ የሚከተለውን እንደሚመስል ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ዳንኤል በርትቶ እንዲያጠና መከርኩት።

**ተግባር ሁለት**

ተማሪዎች ከቤተሰባቸው ወይም ከሚያውቁት ሰው ከሚከተሉት በየትኛው ሙያ እንደተሳተፈ እንዲናገሩ ማድረግ፣ ቃላቱም፡- ሀኪም፣ ወታደር፣ መምህርና ሾፌር ናቸው። ተማሪዎች የተናገሩትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ግሶችን ማለማመድ ይቻላል።

ዮናስ ወታደር ሆነ።

ሚፍታህ መምህር ሆነ።

ገረመው ሀኪም ሆነ።

መገርሳ ሾፌር ሆነ።

በሌላ መንገድ በሁለት ተማሪዎች መካከል የሚደረገውን ምልልስ እንዲቀርብ በማዘዝ የተማሪዎችን ንግግር በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ግስን ማለማመድ ይቻላል። የተማሪዎቹ ንግግር የሚከተለውን ይመስላል።

ወንድማገኝ፣ ተፈራን አይተሀል?

ኩመራ፣ ተፈራ እቤቱ ውስጥ አለ።

እላይ የቀረቡ ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ግሶችን እንዲያመለክቱ ማለማመድ፤ በመጨረሻም አንድ ቃል በግስ የቃል ክፍል ለመመደብ የመሆን፣የመኖር፣ ሌሎች ተግባራትን የሚያመለክቱ እንዲሁም በዐረፍ ተነገር ውስጥ በስተ መድረሻ በመግባት ዐረፍተ ነገሩ የተሟላ ሀሳብ እንዲሰጥ የሚያደርጉ መሆናቸውን ለተማሪዎች ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

## ክፍለ ትምህርት ሶስት፤ ቅጽል

በዚህ ክፍለ ትምህርት ከቃል ክፍሎች ቅጽልን በመውሰድ የሚቀርብ ነው፡፡ በክፍለ ትምህርቱም የቅጽል ምንነት፣አንድ በቅጽል የቃል ክፍል ለመመደብ ማሟላት ያለበትን መስፈርትና ቅጽሎች ተግባራቸው ምን እንደሆነ የሚቀርብበት ነው፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ 2፡00**

**ተግባር አንድ**

ሁለት መጽሐፍ ወደ ክፍል ይዞ ወደ መማሪያ ክፍል በመምጣት መጽሐፎቹን ለተማሪዎች ተራ በተራ በማሳየት ያሉበትን ደረጃ እንዲገልጹ ማድረግ፤ ከተማሪዎቹ የሚገኘው መልስ የሚከተሉትን እንደሚመስሉ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

<u>አሮጌ</u> መጽሐፍ

<u>አዲስ</u> መጽሐፍ

የተገኘውንም መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በቅጽል የቃል  ክፍል የሚመደቡትን ከላይ በቀረበው መንገድ እንዲያመለክቱ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

በሌላ መንገድ መምህሩ ረጅምና አጭር ሰው የሚያመለክት ስዕል በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሳል ለስዕሎቹ ቁጥር በመስጠት በተራ ቁጥር አንድ የተወከለው ምን እንደሚያመለክት፣በተራ ሁለት የተወከለው ምን እንደሚያመለክት ተማሪዎች እንዲገልጹ ማድረግ፣የተማሪዎችን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ቅጽሎችን ከስራቸው እንዲያስምሩ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

1. ረጅም ሰው
2. አጭር ሰው

አሁንም ሁለት የተለያየ መጠን ያላቸውን ወንበሮች የሚያመለክቱ ስዕሎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሳል የወንበሮቹን መጠን እንዲናገሩ  ማዘዝ፣ ከተማሪዎች የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ቅጽሎችን እንዲለዩ ማለማመድ ይቻላል፡፡

1.ትልቅ ወንበር

2.ትንሽ ወንበር

**ተግባር ሁለት**

ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ የተለያዩ ሰዎች ያላቸውን ባህርይ በአእምሮአቸው እንዲያስቡ ማዘዝ፡፡ ከዚያም ያስታወሱትን ሰዎች ባህርይ እንዲናገሩ ማድረግ፣ ከተማሪዎቹ የተገኘውን መልስ በራሳቸው ከስራቸው በማስመር ቅጽሎችን በማመልከት በሚከተለው መልኩ እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

<u>ታታሪ</u> ሰው

<u>አስተዋይ</u> ሰው

<u>ንፉግ</u> ሰው

<u>ውሸታም</u> ሰው

<u>ደግ</u> ሰው

ተማሪዎች ከዩኒፎርማቸው ስር የለበሱትን በማመልከት የተማሪዎቹ ልብስ ምን አይነት መልክ እንዳለው እንዲገልጹ በማድረግ ቅጽሎችን ማለማመድ ይቻላል፡፡ የመምህሩ ጥያቄና የተማሪዎች መልስ የሚከተለውን ሊመስል ይችላል፡፡

መምህር፤ የአመንሲስ ሸሚዝ መልኩ ምንድን ነው?

ተማሪ፤ ነጭ

መምህር፤ የማሞ ሹራብ መልኩ ምንድን ነው?

ተማሪ፤ ቀይ

መምህር፤የለሚሳ ከነቴራ መልኩ ምንድን ነው?

ተማሪ፤ ጥቁር

የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን ምስል የያዘ ፖስተር ወደ ክፍል ይዞ በማምጣት ከፖስተሩ ላይ እያንዳንዱን በማመልከት የጓሮ አትክልቶቹን መልክ እንዲናገሩ ማድረግ፣ የተገኘውንም መልስ በሚከተለው መልኩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡

| የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች አይነት | የተማሪዎች መልስ |
|---|---|
| ቲማቲም | ቀይ |
| ቃሪያ | አረንጓዴ |
| ሙዝ | ቢጫ |
| ብርቱኳን | ቢጫ |
| ጎመን | አረንጓዴ |
| ሽንኩርት | ቀይ |
| ሽንኩርት | ነጭ |

ከዚህ ልምምድ በመነሳት ተማሪዎች ቅጽሎችን እንዲለዩ ማድረግ ይቻላል፡፡ በመጨረሻም መምህር ቅጽሎች ስምን ቀድመው በመግባት ስምን ከመጠን፣ከመልክ፣ከባህርይ ወዘተ አንጻር እንደሚገልጹ ማስገንዘብ፤ አገባባቸውም ከስም በፊት እንደሆነ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከስም በፊት የገባ ሁሉ በቅጽል የቃል ክፍል ይመደባል ማለት እንዳልሆነ ምሳሌ በመስጠት ማስገንዘብ ይቻላል፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፤ መስተዋድድ

በዚህ ክፍል የመስተዋድድ ምንነት፣ መስተዋድዶች በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸው ተግባር ይቀርባል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ 2፡00**

**ተግባር አንድ**

መምህር አንድ ተማሪ በማስነሳት ከመማሪያ ክፍል ወጥቶ መነሀሪያ ደርሶ እንዲመጣ ቢታዘዝ በየት በኩል አድርጎ ደርሶ እንደሚመጣ እንዲናገር ማዘዝ፣ከተማሪው የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ከቀረበው ሀሳብ መስተዋድዶችን ለይተው እንዲያመለክቱ

በማለማመድ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከተማሪው የተገኘ መልስ የሚከተለውን ሊመስል እንደሚችል ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ክፍል እንደ ወጣሁ ወደ ግራ እታጠፍና ወደ መውጫው የሚወስደውን መንገድ እይዛለሁ፡፡ ልክ መውጫያው በር ጋር እንደ ደረስኩ ወደ ቀኝ ታጥፌ ዋናውን መንገድ እይዛለሁ፡፡ ጥቂት ከተጓዝኩ በኋላ በዞኑ ፍርድ ቤት በኩል ወደ ታች በመውረድ ወደ ቀኝ ከታጠፍኩ በኋላ ዋናውን የአስፋልት መንገድ ይዤ ወደ ላይ እወጣለሁ፡፡ ልክ የዞን ምክር ቤት አጠገብ እንደ ደረስኩ ቀጥታ ወደ ፊት በመሄድ የሻምቡ ከተማ መነህሪያ እደርሳለሁ፡፡ ከዚያም አሁን በሄድኩበት አቅጣጫ ተመልሼ ወደ ክፍሌ እገባለሁ፡፡

**ተግባር ሁለት**

ለሶስት ተማሪዎች መምህሩ በሚከተለው መልኩ ጥያቄዎችን በማቅረብ መስተዋድዶችን ማለማመድ ይቻላል፡፡

መምህር፤ የአብሼ ገርባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአራቱም አቅጣጫ የሚያዋስኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ዘርዝር፡፡

ተማሪ፤ በሰሜን፣የዞን ፍርድቤት

በደቡብ፣የሻምቡ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት

በምስራቅ፣የሻምቡ ካቶሊክ ትምህርት ቤት

በምዕራብ፣የመብራት ሀይል መስሪያቤት

መምህር፤ የሻምቡ ሆስፒታል የሚያዋስኑ መስሪያቤቶችና ተቋማት ጥቀስ፡፡

ተማሪ፤ በምስራቅ፣የሻምቡ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም

በምዕራብ፣የእርሻ ሰብል መጋዘንና መስሪያቤት

በሰሜን፣የአውራ ጎዳና ካምፕ

በደቡብ፣ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ሻምቡ ቅርንጫፍ

መምህር፤የሻምቡ ጤና ጣቢያ የሚያዋስኑ መስሪያ ቤቶችና ተቋማት ጥቀስ

ተማሪ፤ በሰሜን፣የሻምቡ ከተማ ትምህርት ቢሮ

በደቡብ፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ቤተክርስቲያን

በምስራቅ፣ የከተማው አስተዳደር መስሪያቤት

በምዕራብ፣ የሆሮ ወረዳ ምክርቤት

ከተማሪዎች የተገኘውን መልስ መሰረት በማድረግ መስተዋድዶችን ለይተው ስር እንዲያሰምሩ በማድረግ መስተዋድድ ማለማመድ ይቻላል፡፡

**ተግባር ሶስት**

መምህሩ ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ከተማሪዎች የተገኘውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ መስተዋድድ ማለማመድ ይቻላል፡፡

መምህር፤ወደ ገበያ ከነማን ጋር ሂደሽ ታውቂያለሽ?

አያንቱ፤ ከእናቴ ጋር

ከእህቴ ጋር

ከወንድሜጋር

መምህር፤የዞኑ ስፖርት ውድድር ሲካሄድ ወደ ስታድየም ከማንጋር ሄደህ ታውቃለህ?

ገላና፤ ከአባቴ ጋር

ከጓደኛዬጋር

ከአጎቴጋር

መምህር፤ ዘመድ ጥየቃ ሆስፒታል ከማን ጋር ሄደህ ታውቃለህ?

በቀለ፤ ከጎረቤታችንጋር

ከአባቴጋር

ከእናቴጋር

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ቁሶችን ወደ ክፍል ይዞ በመምጣት በወንበር ላይ በማስቀመጥ ወይም ከወንበር ስር በማስቀመጥ ቁሶቹ የተቀመጡበትን እንዲናገሩ በማድረግ መስተዋድድ ማለማመድ ይቻላል፡፡

በመጨረሻ መምህሩ መስተዋድዶች በዐረፍተ ነገር ውስጥ ገብተው ሲታዩ ብቻቸውን ትርጉም እንደማይሰጡ፣የቃላት እርባታም ሆነ ምስረታ የሚውሉ ጥገኛ ምዕላዶችን እንደማያስጠጉ ምሳሌዎችን በማቅረብ ማስረዳት፣መስተዋድዶች ትርጉም የሚኖራቸው ከስም ጋር ተቀናጅተው ሲቀርቡ መሆኑን ማስገንዘብ ይቻላል፡፡ መስተዋድዶች ቦታን አቅጣጫን ወዘተ የሚያመለክቱ መሆናቸውን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## ክፍለትምህርት አመምስት፤ ተውሳከ ግስ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተውሳከ ግስ ከቃል ክፍል አንዱ እንደሆነና ተውሳከ ግስ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖረው ተግባር ይቀርባል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበ ጊዜ 2፡00**

**ተግባር አንድ**

የሚከተሉትን ተግባራት ተማሪዎች እንዲፈጽሙ በማዘዝ ተውሳከ ግስ ማለማመድ ይቻላል፡፡ ሶስት ተማሪዎች በሚከተለው መልኩ ጭውውት እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎች ጭውውቱን ሲያቀርቡ እያንዳንዳቸው የሚናገሩትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ከንግግራቸው ተውሳከ ግስ እንዲለዩ ማድረግ ይቻላል፡፡

ብስራት፤ጤና ይስጥልኝ ይህ ልጅ አልተሻለውም?

አያንቱ፤ አልተሻለውም፤ክፉኛ ታሟል፡፡

ብስራት፤ ውይ ምንኛ ያሳዝናል?

**ተግባር ሁለት**

ሁለት ተማሪዎች አንድ መኪና ካሰቡበት ቦታ መድረስ አለመድረሱን ለማወቅ በስልክ የሚያደርጉትን ምልልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተውሳከ ግሶችን ማለማመድ ይቻላል፡፡ ከሁለቱ

ተማሪዎች የሚቀርበውን ንግግር ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች በተውሳከ ግሶቹ ቃላት ስር ሌሎች ተማሪዎች ስር እንዲያሰምሩ በማድረግ እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሚፍታህ፤ መኪናው ደረሰ?

ገላና፤ ገና አልደረሰም፡፡

ሚፍታህ፤ ቶሎ ይደርሳል ጠብቅ፡፡

ገላና፤ እሽ

ከላይ ከቀረቡ ልምምዶች በተጨማሪ መምህሩ ተውሳከ ግስ ከቃል ክፍሎች አንዱ መሆኑን፣ ከሌሎች ቃላት አንጻር ሲታይ ተውሳከ ግሶች በጣም ጥቂት እንደሆኑ፣በዚህ ምክንያት ሌሎች ቃላትና ሀረጋት የተውሳከ ግስ ተግባር እንደሚፈጽሙ ምሳሌ በመስጠት ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ቅጽሎች ስምን እንደሚገልጹ ሁሉ ተውሳከ ግሶችም ግስን ከቦታ ከሁኔታዎች አንጻር ሊገልጹ እንደሚችሉ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፤ዓረፍተ ነገር

በዚህ ክፍል የዓረፍተ ነገር ምንነት፣ዓረፍተ ነገር ከሁለት ዋና ተዋቃሪ አካላት እንደሚመሰረት እነሱም ምንና ምን እንደሆኑ ፣በውስጡም ሙሉ ሀሳብ የሚተላለፍበት መሆኑ ይቀርባል፡፡

**ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ 2፡00**

**ተግባር አንድ**

በመምህርና በተማሪ መካከል የተለያዩ ክስተቶችን በተመለከተ ከሚቀርብ ምልልስ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

መምህር፤ በ1ኛ ሴምስቴር ከክፍላቸው ጥሩ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ሲሸለሙ ንግግር ያደረጉ ሰው ማን ናቸው?

ተማሪ፤የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር

መምህር፤ርዕሰ መምህር ምን አቀረቡ?

ተማሪ፤የ1ኛ ሴምስቴር አጠቃላይ ሪፖርት አቀረቡ፡፡

በመቀጠል ተማሪው የተናገረውን አንድ ላይ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ የሚከተለውን ጥያቄ ለተማሪዎች በማቅረብ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ እንዲለዩ ማለማመድ ይቻላል፡፡

የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር የ1ኛ ሴምስቴር አጠቃላይ ሪፖርት አቀረቡ፡፡ መምህር፤ ሪፖርቱን ያቀረቡ ሰው ማን ናቸው?

ተማሪ፤የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር

መምህር፤ ምን አደረጉ?

ተማሪ፤የ1ኛ ሴምስቴር አጠቃላይ ሪፖርት አቀረቡ፡፡

**ተግባር ሁለት**

ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው የተደረገውን የመምህራን ስፖርት ውድድር እንዲያስታውሱ በመንገር ከመምህራኖቻቸው መካከል በተካሄደው ውድድር ላይ በጥሩ ሁኔታ የተጫወተውን እንዲጠቅሱ ማድረግ፣ መምህራኑ በጥሩ ሁኔታ መጫወት የሚችሉትን የጫወታ አይነት በመጥቀስ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ማለመማድ ይቻላል፡፡

የሂሳብ መምህራችን እግር ኳስ መጫወት ይችላሉ፡፡

የኬምስትሪ መምህራችን መረብ ኳስ መጫወት ይችላሉ፡፡

የሰውነት ማጎልመሻ መምህራችን የቅርጫት ኳስ መጫወት ይችላሉ፡፡

ከተማሪዎች የተገኘውን መልስ መሰረት በማድረግ መምህሩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ከተማሪዎች በሚገኘው መልስ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

መምህር፤ከመምህራኖቻችሁ እግር ኳስ መጫወት የሚችል ማን ነው?

ሰይድ፤ የሂሳብ መምህራችን

መምህር፤ የኬምስትሪ መምህራችሁ ምን መጫወት ይችላሉ?

ወንድማገኝ፤መረብ ኳስ መጫወት ይችላሉ፡፡

መምህር፤ በሶስተኛ ደረጃ የተገለጹት መምህር የምን መምህር እንደሆኑ ከገለጻችሁ በኋላ ምን መጫወት እንደሚችሉ ተናገሩ፡፡

ኩመራ 1. የሰውነት ማጎልመሻ መምህር

2. ቅርጫት ኳስ መጫወት ይችላሉ፡፡

በመጨረሻም ከላይ በተግባር አንድና ሁለት የቀረቡትን መሰረት በማድረግ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጎች ስር እንዲያሰምሩ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡ መምህሩም ስማዊ ሀረግ መሪውቃል ስም እንደሆነ ግሳዊ ሀረግም መሪውቃል ግስ እንደሆነ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ሌሎች ተዋቃሪ አካላት በነዚህ ሁለቱ አካላት ውስጥ ሊካተቱ እንደሚችሉ ምሳሌ በማቅረብ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**ተግባር ሶስት**

ዓረፍተ ነገር የስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ቅንጅት መሆኑን፣ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብ ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን ማስገንዘብ ይቻላል፡፡

የተለያዩ ቃላትን አዘበራርቆ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች አስተካክለው ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡- ሀ. ወደ ሄደ ትምህርት ቤት ተፈራ፡፡ (ተፈራ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡)

ለ. ሀዊ በላች ምሳዋን፡፡( ሀዊ ምሳዋን በላች፡፡)

በመጨረሻም የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ከምሳሌዎቹ በመነሳት ተማሪዎች የራሳቸውን ምሳሌ በመስጠት ዓረፍተ ነገር መገንባት እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

## አባሪ 2

# ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሰዋስው ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና (50%)

**ስም-------------------------------ክፍል---------ተራ ቁጥር----------ጾታ----------**

ፈተናው የሚጀመርበት ሰዓት 2፡30

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ 1፡00 ሰዓት

**አጠቃላይ መመሪያ፤** ይህ ፈተና በሻምቡ አብሼ ገርባ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ዘዴዎች የተማሪዎችን ሰዋስው እውቀት በማጎልበት ረገድ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመፈተሽ እየተካሄደ ላለው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀ ነው፡፡ ፈተናው አራት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል አስር የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሶስት የባዶ ቦታ ሙላ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ የሶስተኛው ክፍል አምስት የአዛምድ ጥያቄዎችን ሲይዝ አራተኛው ክፍል ሁለት ተዘበራርቀው ያሉ ቃላት አስተካክሎ ዓረፍተ ነገር መመስረትን ይዟል፡ ፡

በየክፍሎቹ ለቀረቡ ጥያቄዎች ሌሎች ንዑሳን መመሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን እንደየ ንዑሳን ክፍሎች መመሪያ አጠያየቅ ተገቢውን መልስ ስጥ/ስጭ፡፡

***ማሳሰቢያ፤*** *ፈተናውን ከመጀመርህ/ሽ አስቀድሞ የፈተናው ገጾች ብዛት አምስት መሆናቸውን አረጋግጥ/ጭ፡፡*

## ክፍል አንድ፤የምርጫ ጥያቄዎች

***መመሪያ አንድ፤ የሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ክፍሎችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘ ሆሄ በመምረጥ ከጥያቄዎች ፊትለፊት በተዘጋጀው መልስ መስጫ ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ሙይ፡፡*(2%)**

------------1. የሚከተለውን ምልልስ በትኩረት በማንበብ በምልልሱ ውስጥ ከስሩ የተሰመረበት በየትኛው የቃል ክፍል እንደሚጠቃለል ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡

አልማዝ፤ልጅሽ ተሻለው?

ማርታ፤ ምን ባክሽ **ክፉኛ** ታሟል፡፡

ሀ. በስም ሐ. በተውሳከግስ

ለ. በግስ መ. በቅጽል

-----------2. ከዚህ በታች ከቀረቡት ሀሳቦች **ቅጽልን** በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቅጽሎች ከስም በፊት በመግባት ስምን ከመጠን፣ከባህርይ አኳያ ይገልጻሉ፡፡

ለ. ግሶች ከቅጽል በፊት በመግባት ቅጽልን ከቦታ፣ከጊዜ አኳያ ይገልጻሉ፡፡

ሐ. በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ሆነው ያገለግላሉ፡፡

መ. ከመስተዋድድ ጋር በመግባት መስተዋድድን ከተለያየ አንጻር ይገልጻሉ፡፡

-----------3. አንድ ቃል በስም የቃል ክፍል ለመመደብ ከቀረቡት አማራጮች እንደመስፈርት **የማያገለግለው** የቱ ነው?

ሀ. -ኦች የሚለውን ቅጥያ ምዕላድ የሚያስጠጋ መሆን አለበት፡፡

ለ. -ኡ የሚለውን ቅጥያ ምዕላድ የሚያስጠጋ መሆን አለበት፡፡

ሐ. -ኝ የሚለውን ቅጥያ ምዕላድ የሚያስጠጋ መሆን አለበት፡፡

መ. -ኤ የሚለውን ቅጥያ ምዕላድ የሚያስጠጋ መሆን አለበት፡፡

-----------4. ከቃል ክፍሎች ለቃላት እርባታም ሆነ ምስረታ የማይውለው የትኛው ነው?

ሀ. ግስ ሐ. ስም

ለ. መስተዋድድ መ. ቅጽል

------------5. ከዚህ በታች የተለያዩ ሀረጋት ተዘርዝረዋል፡፡ ከስራቸው ከተሰመረባቸው **በግስ** የቃል ክፍል የሚጠቃለለው የቱ ነው?

ሀ. አጭር ሰው ሐ. ከእህቱ ጋር

ለ. ጥቁር በሬ መ. ወደቤቱ ሄደ

-----------6. መምህር፤ ዳንኤልን በመጥራት እስቲ ከቤታችሁ ወደ ትምህርት ቤት ስትመጣ በየት አድርገህ እንደምትመጣ ንገረን?

ዳንኤል፤ከቤታችን **እንደ**ወጣሁ ዋናውን መንገድ ለመያዝ **ወደ**ታች እወርዳለሁ፡፡ ዋናውን መንገድ ከያዝኩ በኋላ ወደፊት በመጓዝ ጤና ጣቢያው ጋር ስደርስ ወደቀኝ ታጥፌ እዚህ እደርሳለሁ፡፡

እላይ ከቀረበው የዳንኤል ንግግር ውስጥ ከስራቸው የተሰመረባቸው በየትኛው የቃል ክፍል ይጠቃለላሉ?

ሀ. በመስተዋድድ ሐ. በስም

ለ. በተውሳከግስ መ. በቅጽል

-------------7. ከሚከተሉት ቃላት አንዱ በተውሳከ ግስ የቃል ክፍል ይጠቃለላል፡፡

ሀ. በሰለ ሐ. ወደ

ለ. ቶሎ መ. ሰውነት

------------8. ከሚከተሉት ቃላት አንዱ በስም የቃል ክፍል ይመደባል፡፡

ሀ. ደግ ሐ. ገና

ለ. በላ መ. ፈረስ

9. አባትና ልጅ ቁጭ ብለው በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የሚተላለፈውን በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የሚገኘውን ጭላዳ ዝንጀሮ እየተመለከቱ፣

ልጅ፣ አባ እነዚህ ሁሉ ዝንጀሮዎች በአንድ ላይ ሲጠሩ ምን ይባላሉ?

አባት፣------------------------ ተብለው ይጠራሉ፡፡

ሀ. ዝንጀሮዎቻችን

ለ. ዝንጀሮ

ሐ. የዝንጀሮ መንጋ

መ. ዝንጀሮኣችን

10. ልጅ ብሎ ልጁ ካለ ዶሮ ብሎ ዶሮዩ ይላል፡፡ ዶሮዩ እንዲል ያደረገው ምክንያት ቃሉ በ--------- የጨረሰ በመሆኑ ነው፡፡

ሀ. በሳድስ ሆሄ

ለ. በተናባቢ

ሐ. በአናባቢና በተናባቢ

መ. በአናባቢ

## ክፍል ሁለት፤ ባዶ ቦታ ሙላ ጥያቄዎች

***መመሪያ ሁለት፤ የሚከተሉት ጥያቄዎች ስስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ እንዲሁም ዓረፍተነገርን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከቀረቡት ምልልሶች ከስራቸው የተሰመረባቸው ሀረጋት በየትኛው የሀረግ ክፍል እንደሚመደቡ በቀረበው ባዶ ቦታ ላይ መልስ/መልሺ፡፡(4%)***

11.መምህር፤ ባለፈው የአማርኛ መምህራችሁ የፈጸሙትን ተግባር ተናገር፡፡

ተማሪ፤ የኤች አይቪ ኤድስ በሽታ ለመከላከል በተሰጠው ትምህርት ላይ የአማርኛ መምህራችን ኤች አይቪ ኤድስን በተመለከተ ግጥም አነበቡ፡፡

መምህር፤ግጥሙን ያነበቡት ማን ናቸው?

ተማሪዎች፤<u>**የአማርኛ መምህራችን**</u> ናቸው፡፡

ከቀረበው ምልልስ ከስሩ የተሰመረው ----------------------------ሀረግ ይባላል፡፡

12.አለማየሁ፤ ትላንት ከአዲስ አበባ የመጣው ልጅ የት ሄደ?

ትዕግስት፤ <u>**ወደ ባህር ዳር ሄደ፡፡**</u>

ከቀረበው ምልልስ ከስሩ የተሰመረው---------------------------ሀረግ ይባላል፡፡

13.ቃል ወይም የቃላት ስብስብ ሆኖ ሀሳብን በተሟላ መንገድ የሚያስተላልፈው------------------ ተብሎ ይታወቃል፡፡

## ክፍል ሶስት፤ የአዛምድ ጥያቄዎች

**መመሪያ ሶስት፤ ከታች የተዘረዘሩትን ቃላት ከግርጌያቸው በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባሉ ክፍት ቦታዎች የሀሳብ ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ በማስገባት አሟሉ፡፡(2%)**

| | |
|---|---|
| ተሰኝቷል | ልጅ |
| ወደ | ምንኛ |
| ባለገ | እልኸኛ |
| ተናካሽ | እልህ |

14. --------- ውሻ ያለበት ግቢ በሌባ አይደፈርም፡፡

15. በሰርጉ እለት ነጭ ልብስ ባለመልበሱ ቅር ------------፡፡

16. የሀይሉ ልጅ --------- ያሳዝናል፡፡

17. እልኸኛ ------------------ተው ቢሉት አይሰማም፡፡

18. ገና ከሩቁ ሳያት ዘላ-------------- ቤቷ ገባች፡፡

## ክፍል አራት፤ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክሎ መጻፍ

**መመሪያ አምስት፤ ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክላችሁ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡(4%)**

19. እየሄደ አስረሱ ወደ ትምህርትቤት ነው፡፡

20. አሰጣች ብዙአየሁ የወንድሟን አጥባ ልብስ፡፡

## አባሪ 3

# በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች፡- የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው መማር/ማስተማር ሂደት ላይ ጥናት ለማካሄድ ነው፡፡ ጥናቱ በተለይ ከዝርዝር ወደ ጥቅልና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ዘዴዎችን ቀላቅሎ ሰዋስውን ማስተማር የተማሪዎችን ሰዋስው መማር ፍላጎት በማጎልበት ስላለው ሚና ለሚካሄድ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው አራት አራት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አማራጭ መልሶች በቁጥር የተሰየሙ ሲሆኑ ቁጥሮቹም የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃ ይወክላሉ፡፡ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ሲደረደሩ በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

4 = በጣም እስማማለሁ

3 = እስማማለሁ

2 = አልስማማም

1 = በጭራሽ አልስማማም

ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረቡትን ዝርዝር ጥያቄዎች በማንበብ ያንተን/ቺን ሀሳብ ወይም እምነት ያንጸባርቃል የምትለውን/ይውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንድ ምርጫ በመምረጥ ከእያንዳንዱ ዓረፍተነገር ፊትለፊት ይህን (X) ምልክት በማድረግ ስምምነትህን/ሽን አመልክት/ቺ፡፡ አንተ/ቺ የምትሰጠው/ጪው መልስ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ በተቻለ መጠን የምትሰጣቸው/ጫቸው መልሶች በትክክል ያንተን/ቺን ስሜትና እምነት የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ አደራ እላለሁ፡፡ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡ መልስህ/ሽ በምስጢር ይያዛል፡፡

ስለቀና ትብብርህ/ሽና ስለታማኝነትህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ።

| ተራ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | የአማርኛ መምህራችን የሰዋስው ህጎችን በራሴ እንድደርስበት ሲያደርጉና እሳቸውም ሲነግሩኝ ደስይለኛል። | | | | |
| 2. | በቃል ልምምድ ጊዜ መምህሬ የሰዋስው ስህተቶችን ሁልጊዜ እያረሙ ሲያስተምሩ ደስይለኛል። | | | | |
| 3. | ሰዋስውን ስማር መምህሬ በቅርጽና በመልዕክት ላይ ትኩረት ሰጥተው ቢያስተምሩ ምርጫዬ ነው። | | | | |
| 4. | መምህሬ ሰዋስው ሲያስተምሩ ምሳሌዎችን እየሰጡ ከምሳሌዎቹ መዋቅራዊ ህግጋትን እየለዩ ሲያመለክቱኝ ያስደስተኛል። | | | | |
| 5. | ተፈጥሯዊ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሰዋስው ብማር የሰዋስው እውቀቴን ያጎለብትልኛል። | | | | |
| 6. | መምህሬ ሰዋስውን ሲያስተምሩ በቃል ከማስረዳት በተጨማሪ በአውድ እንድጠቀም ሲያደርጉ ያስደስተኛል። | | | | |
| 7. | ሰዋስውን ለመማርና ለማወቅ ከመምህር ተኮር ይልቅ ተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ያስደስተኛል። | | | | |
| 8 | መምህሬ ፍጹም የሰዋስው ትክክለኛነት ላይ ቢያተኩሩ እመርጣለሁ። | | | | |
| 9 | መምህሬ ምሳሌዎችን እያቀረቡ ከምሳሌዎቹ በመነሳት በራሴ የሰዋስው ህግ እንድደርስበት የሚያደርግ የማስተማሪያ ዘዴ እውቀቱና ብቃቱ ሲኖራቸው ሰዋስው የመማር ፍላጎቴን ያሳድጋል። | | | | |
| 10 | መምህሬ ለመግባባት የሚያስችል የሰዋስው እውቀት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለማስጨበጥ ከሚሰጡኝ ምሳሌ በመነሳት የራሴን ምሳሌ እየሰጠሁ እንድማር የሚያግዙ የግንዛቤ ማሳደጊያ መልመጃዎችን በማቅረብ ቢያስተምሩ እመርጣለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | ሰዋስው ስማር መምህሬ የዓረፍተነገርና የቃል ክፍሎችን መዋቅር በመተንተን  ሲያስተምሩና ከሚሰጡኝ ምሳሌ በመነሳት የራሴን ምሳሌ በማዋቀር ህግጋትን እንድለይ ሲያደርጉ የሰዋስው እውቀቴን ከፍ ያደርግልኛል፡፡ | | | | |
| 12 | ሰዋስውን ሁልጊዜ ህግጋትን በመተንተን  ከመማር ከቀረቡ ምሳሌዎች በመነሳት በራሴ ምሳሌ በመስጠት ህግጋትን እያወጣሁ  መማር የሰዋስው እውቀቴን ያሳድግልኛል፡፡ | | | | |
| 13 | መምህሬ ሰዋስውን እንደሂደት ሳይሆን እንደግብ ቢያስተምሩ እመርጣለሁ፡፡ | | | | |
| 14 | ቋንቋዬን ለማሻሻል መምህሬ የሰዋስው ህጎችን እያሰብኩ ቋንቋውን እንድጠቀም ሲያደርጉ ደስይለኛል፡፡ | | | | |
| 15 | ከምሳሌዎች በመነሳት የራሴን ምሳሌ በመስጠት ህግጋት ላይ በመድረስ ሰዋስውን የመማር ሂደት በራስ መተማመኔን ከፍ ያደርግልኛል፡፡ | | | | |

*አባሪ 4*

## *በቅድመና በድህረ ሙከራ ፈተናዎች የተገኘው ውጤት*

| | ቅድመ ሙከራ | | | ድህረ ሙከራ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተራ ቁጥር | 50% | ተራ ቁጥር | 50% | ተራ ቁጥር | 50% | ተራ ቁጥር | 50% |
| *1* | *20* | *16* | *10* | *1* | *24* | *16* | *26* |
| *2* | *32* | *17* | *38* | *2* | *38* | *17* | *42* |
| *3* | *22* | *18* | *10* | *3* | *36* | *18* | *20* |
| *4* | *31* | *19* | *27* | *4* | *36* | *19* | *32* |
| *5* | *16* | *20* | *20* | *5* | *20* | *20* | *35* |
| *6* | *28* | *21* | *30* | *6* | *32* | *21* | *37* |
| *7* | *40* | *22* | *45* | *7* | *46* | *22* | *46* |
| *8* | *21* | *23* | *26* | *8* | *28* | *23* | *32* |
| *9* | *14* | *24* | *28* | *9* | *22* | *24* | *35* |
| *10* | *12* | *25* | *23* | *10* | *20* | *25* | *28* |
| *11* | *21* | *26* | *26* | *11* | *28* | *26* | *32* |
| *12* | *22* | *27* | *18* | *12* | *26* | *27* | *28* |
| *13* | *24* | *28* | *16* | *13* | *30* | *28* | *26* |
| *14* | *34* | *29* | *26* | *14* | *38* | *29* | *32* |
| *15* | *20* | *30* | *18* | *15* | *28* | *30* | *26* |